See discussions, stats, and author profiles for this publication at: https://www.researchgate.net/publication/361594142


# □□ □□□□□□ □□□□ □ □ □□□□□□ □□□□ □□□□ □□□□ □□□ □□

**Book** · June 2022

CITATIONS
0

READS
39

1 author:



Ashenafi Legesse Segni
University of South Africa

**11** PUBLICATIONS **0** CITATIONS

SEE PROFILE

All content following this page was uploaded by Ashenafi Legesse Segni on 28 June 2022.

The user has requested enhancement of the downloaded file.

# ገ ዳ

## የኢትዮጵያ ስልጣኔ

**ጸሀፊ፡**

**አሸናፊ ለገሰ ሠኚ**

E-mail ashenafi.legese@ju.edu.et

**ስልክ ቁ. 0911-615648**

ግንቦት፣ ፳፻፻፻

ጂማ፣ ኢትዮጵያ

*© የጸሀፊው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።*

*የመጀመሪያው እትም ግምቦት፣ 2011፣* ግርማ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ

*ሁለተኛው እትም ታህሳስ፣ 2012፣* ሲንግተን ማተሚያ ቤት፣ ጂማ፡ ኢትዮጵያ

*@ማንኛውንም ሀሳብ አስተያየት እንዲሁም ገንቢ ጥቆማቹን በአድራሻችን ያድድርሱን*

# ማውጫ

**መቅድም** ....7

**እልማ ገልማ አባ ገዳ** ....8

**ትምህርት 1**....13

**የሠፉ ሥሪ-አት** ....13

1.1 መግቢያ ....13

**ስእል 1፡ ኡማ ኡማማ እና ኡማታ** ....15

**ስእል 2: ሴቶች በባህላዊ ልብስ በሲቄ ስርአት** ....16

1.2 ባህል ....16

*1.2.1 የጋብቻ ሥነ-ሥራአት*....20

*1.2.3 ያለ ምክር ያገቧት ያለምክክር ይፈቷቷል*....20

*1.2.4 ሶዳ /አማች/* ....21

*1.2.5 ሶዳና እሳት ከሩቅ*....21

**ስዕል 4: የሙሽሪት የሽኝት ጊዜ**....22

1.3 ቃሉና ቃሊቲ ....22

1.4 የአባቶች በአል (ቦረንቲቻ)....ERROR! BOOKMARK NOT DEFINED.

1.5 የእናቶች በአል (አቴቴ) ....ERROR! BOOKMARK NOT DEFINED.

1.6 አያና ዋዳጃ ....ERROR! BOOKMARK NOT DEFINED.

1.7 የምስጋና እና የልመና በአል (ኢሬቻ /ኢሬሳ/)....22

1.8 የጎረምሳ ልጆች በአል (ታቦሬ)....23

1.9 የልጃ-ገረዶች ልጆች በአል(ኢንጊጫ)....23

1.11 እህል መድረሻ ጊዜ በአል (ጋኒ) ....24

**ትምህርት 2**....25

**የገዳ እርከንና አኗኗር**....25

2.1. ደበሌ ....26

**ስእል 5፡ ዳባሌ** ....26

2.2 ጋሜ ....27

**ስእል 6፡ ጋሜ**....27

2.3 ፎሌ ....28

**ስእል 7፡ ፎሌ** ........ **29**

2.4 ራባ ........ 30

2.5 ዶሪ ........ 32

**ስእል 9፡ ራባ** ........ **33**

2.6 ገዳ ........ 33

**ስእል 10፡ ገዳ** ........ **34**

2.7 ዩባ ........ 34

**ስእል 11፡ ዩባ** ........ **35**

2.8 ገዳሞጂ ........ 35

**ትምህርት 3** ........ **37**

**የገዳ አስተዳደር ስርአት** ........ **37**

3.1 መግቢያ ........ 37

3.3 ቦኩ ካላቻና ጫጩ........ 37

**ስዕል 12: ቦኩ** ........ **38**

3.3 አራዳ ጂላ........ 39

3.4 አዱላ ገዳ ........ 41

3.5 ሰግለን ያኢ ........ 41

*አባ ቦኩ:* ........ *41*

**ስእል 15፡ አባ ቦኩ** ........ **42**

*አባ ቦኩ1ኛ*........ *43*

*3. አባቦኩ 2ኛ*........ *44*

*4. አባ ሙዳ* ........ *44*

*5. አባ ዱላ* ........ *44*

*6. አባ ሎኒ* ........ *44*

*7. አባ ሴራ*........ *44*

*8. አባ አለንጋ* ........ *44*

*9. አባ ጨፌ* ........ *44*

3.6 የባሊ ርክክብ........ 45

**ስእል 17፡ ማጋላታ እየነፉ የሚቀርቡ ያኢ** ........ **45**

**ስዕል 18: አባ ገዳ ባሊሲሰጥ** ........ **46**

3.7 ጎጌሳ ገዳ ........................................ 48

**ስዕል 19: አዱላ ገዳ ........................................ 49**

**ትምህርት 4 ........................................ 50**

**የፊና ሥርአት ........................................ 50**

4.0 መግቢያ ........................................ 50

**ስዕል 20: የፊና ደረጃዎች ........................................ 51**

4.1 ፈጫሳ ........................................ 51

4.2 ቢቂላ ........................................ 51

4.3 ጉዲና ........................................ 52

4.4 ፉርዲና ........................................ 52

4.5 ጋቢና ........................................ 53

*4.6 ባዳዲና ........................................ 53*

4.6 ዳጋጊና ........................................ 53

**ትምህርት 5 ........................................ 54**

**አያና ........................................ 54**

**ስእል 21፡ አያና ........................................ 54**

5.2 የDHA-U ገዳ ሥርአት ........................................ 55

*5.2.1 ኡርጂ ለሚ (Triangulum) ........................................ 59*

*5.2.2 ኡርጂ ቡሳን (Pleiades) ........................................ 59*

**ስዐል 26: ኡርጂ ቡሳን ከNASA OBSERVATORY ሲታይ ........................................ 60**

*5.2.3 ኡርጂ ባካልቻ (Aldebaran) ........................................ 60*

**ስዕል 27: ኡርጂ ባካልቻ ........................................ 60**

*5.2.4 ኡርጂ አልጋጂማ (Bellatrix) ........................................ 60*

**ስዕል 28: ኡርጂ አላጋጂማ እና ፀሀይ ከቀኝ ወደግራ ከNASA OBSERVATORY ሲታይ ........................................ 61**

*5.2.6 ኡርጂ ቡሳ (Sirius) ........................................ 61*

*5.2.7 ኡርጂ ዋለ (Saiph) ........................................ 62*

**ስዕል 30: ኡርጂ ዋላ ከNASA OBSERVATORY ሲታይ ........................................ 63**

5.3 ወቅቲና ወራት ........................................ 64

ሰንጠረዥ 1፡ አራቱ ወቅቲ ........................................................................................................ 64

ዋቢ መጻህፍት ........................................................................................................ 66

# መቅድም

በዚህ መጽሀፍ ወስጥ ገዳ ከአስተዳደራዊ እና ማህበራዊ እሳቤ በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊና ሳይንሳዊ ይዘቱ እንዱሁም ጥበባዊና መለኮታዊ ገጽታዎችንም ይዳስሳል፡፡ እንደ ጥናታዊ ጽሁፎች ውጤት እና አርጋ dha-ጌቲ አስተምሮት፤ ገዳ ተፈጥሮአዊ የሆነ የስራአት ድምር ውጤት ሲሆን በአምስቱ የሥራአት ምሰሶዎች ላይ ያርፋል (Gadaan Seeraa Yayyaba Shaniin Utubama)፡፡ ዋቃ ገዳን ከአምስት ስርአት ተድምሮ ሰራው፤ ገዲ የሰብን አምሮ ይወክሊሌ፡፡ ትርጓሜውም አምሮ በስርአት የተገነባ የዋቃ ስጦታ ሲሆን ስርአቶቹም:-

1. ፈጣሪ እንደ ፈጠረው የሚያምን
2. በመልፋት /በላቡ/ መብላትን የሚያምን
3. ከጎረቤት ከዘመድ ጋር አብሮ መኖርን የሚያምን
4. ፊና ፊናቹ እንዳለበት የሚያምን ያለው
5. ኢያና ማታ ኢሳ እንዳለው የሚያምን መሉ ሰው ነው ገዳ፡

ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድን ቃዌሳ በአንድ ወቅት እንዲህ ብለው ነበር፡፤ በ1964 ደቡብ ቦረና ድሬ ሊበን ሂጄ ባጋጣሚ ካገኘዋቸው ሰዎች መካከል በአንደበተ ርቱነቱ እንደ ማላ ጋልማ ያስደነቀኝ ሰው የለም፡፡ ማላ ገልማ አባ ገዳ ፤የኦሮሞ ህዝብ ሁሉ በእምነቱ አባ ገዳ ነኝ ብሎ ነው የሚያምነው፡፡ ሂየወቱም በገዳ የተከለለ ሲሆን ከውጭ በመጡ ሀየማኖቶች በሙሉ አያምንም፡፡ ገዳ ካ አዳ ማለት ሲሆን ካ - ማለት እግዛብሄር ሲሆን አዳ ደጋግሞ ስጦታ ነው፡፡ ስለዚ ገዳ ማለት የካ ስጦታ እንደ ማለት ይሆናል፡፡ የዋቃ ስጦታ ደግሞ ሰው ነው ሰው ደግሞ ገዳ ነው፡፡

……. ታዲያ ገዳ ምንድነው …..;

የቻልኩትን ከዋቢ መጽሀፍ ፈልጌ በአምስት ትምህርትም አኑሬዋለው ከመጻፉ ዝለቁ ……..

በወል ቤት ሆኖ ባለ ስምንት ምት (የጸጋዬ ቤት) በሚባለው የተገጠመ ግጥም የሎሬት ጸጋዬ ገ/መድን እልማ ገልማ አባ ገዳ ግጥም ላኑር፡፡ በነገራችን ላይ ይላል ጸጋዬ ወል የሚለው ቃል እጅግ ጥንታው የኩሽ ጥቁር ግብጽ አሩክሪፊክ ቃል ሲሆን የህብር የአንድነት አመልካች ነው ዩናይትድ፡፡ ለምሳሌ ዋሎ (አንድነት)፤ ዋል ዋል፤ ዋልዲያ፤ ዋል አጋ (ታላቅ አንድንት)፤ ወሊንጪቲ፤ ዋሊሶ ዋልቂጤ፤ ዋላይታ (የእውነት አንድነት)፤ ዋለቃየት፤ ዋልማራ ዩናይትድ እንደ ማለት ነው ይላል ሎሬት ጸጋዬ፡፡

## እልማ ገልማ አባ ገዳ

ርቱ ጀማ ብጹ ጀማ

ለካአንተ ነህ

አባ ገዳ ኢልማ ገልማላ

ያዳ ኦሮሞ ሻማ

ዋቃ ጋዲን ናማ ኦሊን

ኦሊ ሱማ አካሱባ

የተሰኘው እንዳ ክሱማ

የተባልከው ፍጹም ጀማ

ለካንተነህ

ኢጋ ኦጋ

ጇጋ ሎጋ

አባ ሳርዳ

አባ ገዳ

አባ ፋርዳ ናባልባሎ

ቅድመ ኦሪት ባህሎ

ያኢ. ቢ.ያ አባ ቃሉ

ቃሉ

የማይቀለበስ ቃሉ

ለካንተነህ

ሴራ አርካ

ኦ.ጋ ገዳ

የአድባር ዋርካ

የአዴ እናቴ የአዴ እሴቴ

የአዴ አቴቴ የአዴ እቴቴ

ጋቲ ሆራ የኩሽ ነዶ

አባ ቦኩ አካሚ ኢ.ዶ

ባእናት ጸሀይ ከላቻ

የምትጠልቅ ባንተ ብቻ

የካም ኢ.ዳ ኢ.ዶ ምድር

ተነባቢ. አስር ሚስጥር

አባ ዋሮ አባ ዋራ

አባ ባሮ አባ ባራ

አባ ካሮ አባ ካራ

የጂቡቲ ጃባጂሾ

የማቅዲሾ ማቃ ዲሾ

የነሙቴሳ ካምባላአ

እንደ ምእራቡ ካምፓላ

ማና ዳላ አካ ማንዳላ

ማቃ ዳላ አካ ማቅዳላ

የፉላኒ ካኖ ዳላ

የምትሰኝ የምታሰኝ

የጎና ቤት አባ ወራ

የላሊ ቤት ላሊ ባራ

የከረዩ አባ ከራ

በጎፈሬህ ስርት ላባ

አዶ አዶዬ ውብ ቀዘባ

አዳ የከለ ተሸላሚ

የአዱ ግምባር ተቀዳሚ

የአዲስ ዘመን መጪው አደይ

አዳ አዱኛን እል እሰይ

የምታሰኝ የምትሰኝ

አዱ አዱኛ አባቢሌ

ያ..አካ..ኪሌ ያ..አባ..ቢሌ

ለካንተነህ

ገዳ የገዳም

የአለም ሰላም

ገዳ ቢሊሱማ ሳቃ

ፋካ ጉራቻ አካዋቃ

የጸሀይ ውስጥ አምላኩ አኒ

ያለበሰችው ድርብ ካኒ

የጥቁር ፈርኦን ልሳን

# ገዳ የኢትዮጵያ ስልጣኔ

አዴ አዳ ጸሀይ ብርሀን

የአዱሊስ አዱኛ ኪዳን

አባ ገዳ አባ በአል

የቅድመ አኩሱማዊት ቃል

የአስርቱ በሮች መሰላል

የማለዳ ንጋት ጸዳል

ያኦሩስ ኦሪሳ ተምሳል

ለካንተነህ

አጋ ኦጋ

ጂጋ ሎጋ

ያኢ ቢያ አባ ቃሉ

የማይቀለበስ ቃሉ

ርቱ ጀማ

የተነባልከው አጋሱማ

አካ አክሱማ

ያዳ ኦሮሞ ሻማ

አባ ገዳ ኢልማ ጋልማ

ለካ አንተነህ

…………….

*(ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድን ቃዌሳ 1964 ድሬ ሊበን)*

…………….

# ትምህርት 1

# የሠፉ ሥሪ-አት



## 1.1 መግቢያ

ዋቃ የሁሉ መጀመርያ ስለሆነ እኛም መነሻችንን እሱን አድረግን፡፡ ስንነሳም ማንጉዶዎች እና ሀዩዎች ስለ ተፈጥሮ፣ ፍጥረትና አፈጣጠር አተያይ በአርጋ ዳጌቲ አስተምህሮት ውስጥ በማስቀመጥ ይሆናል፡፡ይህም እዚች እለም ላይ ምንም ነገር ሳይኖር፤ አለም እራሷ ሳትኖር ትልቅ ውሃ ነበር ይላሉ፡፤ ይህም ውሃው አያና ዋቃ የነበረው ቢሻን ገነማ ኡማ ገነማቲ ይላሉ፡፡ ወደ ሁለትም ተከፍሎ የላይኛው ውሃ እና የታችኛው ውሃም ሆነ፡፡ የላይኛው ውሃም ወደ ሶስት ተከፍሎ አንዱ ሰማይ፤ አንዱ ሰማይ ላይ የሚገቡ ቆሎ (እንደ ፀሐይ፤ ጨረቃና ከዋክብት)፤ አንዱ ደግሞ የሰማይ ውሃ (ደመና) ሆነ፡፡ የታችኛው ውሃም ወደ ሁለት ተከፍሎ አንዱ ምድር ሌላኛው ባህርን ሲሰራ በዚህው ሂደት ውስጥ ሰውም ተፈጠረ፡፡

የኦሮሞ ህዝብ ከኩሽ ህዝብ አንዱ ሲሆን በመካከለኛውና ምስራቃዊ የአፍሪካ ክፍል ከሚኖሩት ወንድሞቹ ጋር ለረጅም ዘመናት የኖረና እየኖረ ያለ ሰፊ ህዝብ ሲሆን የአንድነቱ መገለጫ የሆነውን የጋራ ቋንቋ፤ ባህል፤ ታሪክና አስተምህሮት ያለው ማህበረሰብ ነው፡፡ የህዝቡ እሴትም፡

1. በፈጣሪ የሚያምን ህዝብ እንደነበር፤
2. በእድሜ እርከን የተከፈለ ማህበራዊ ሀላፊነት ያለው፤


3. ዲመክራሲያዊ የስልጣን ሽግግርና ፓለቲካዊ አስተዳደር ያለው፤
4. የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍልስፍና የሆነው የፊና ባለቤት፤
5. የረቀቀ አስትሮኖሚና የብዙ ጥበባት ባለቤት፤

ዋቄፋና ጥንታዊ የኩሽ ህዝብ እምነት ሲሆን የእምነቱ ፍልስፍናም በአንድ አምላክ ማመንና ሰፉ መጠበቅ ነው፡፡ ይህም ፈጣሪውን ዋቃ ብሎ ሲጠራው ዋቃም፡

- ሀያል ነው Guraacha garaa garbaa፤ tokkicha akka dhibbaa (Omin Potent)
- አዳኝ ነው Siwamanu nuu dhuftee (Omine present)
- ዳኛ ነው Yaa'ii malee waa murtee (Omini judje)

በዋቄፋና እምነት አስተምሮት በዋቃ እና በሰው መካከል የአያና ግንኙነት ሲኖር ይህም ሰው ለዋቃ ሁልጊዜ ካ-dha-ና እና ጋአና ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መልኩ የኦሮሞ ህዝብም ሰፉን እየጠበቀ ለፈጣሪው ካ-dha-ና እና ጋአና ሲያቀርብ የኖረ ሲሆን ይሄም ገዳ እንዲጠነክርና የማይናጋ መሰረት ላይ እንዲቆም አድርጎታል፡፡

ሰፉ የመጀመሪያው ሴራ ኡማ ሲሆን በሰዎችና በፈጣሪ፤ በፈጣሪና በፍጡር መካከል የሚኖር ተፈጥሮዊ ህግ ነው፡፡ ሰፉን መጠበቅ ተፈጥሮን መጠበቅ ሲሆን ሆዳ ሰፉ ውስጥ እምነት፤ እውቀት እንዲሁም አስተምሮት ትልቅ ቦታ አላቸው፡፡ ሰፉ የመጀመሪያ ሴራ ያያባ መገናኛ ኡማ፣ ኡማማ እና ኡማታ ስለሆን ሰፉን መጠበቅ የሰዎች ተፈጥሮአዊ ግዴታ ነው፡፡



ስእል 1፡ ኡማ ኡማማ እና ኡማታ

ገዳ ሰፉ ስላለው በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትና ክብር አለው፡፡ ሰፋ አይደነገግሞ ይጠበቃል እንጂ፡፡

ከሰፉ መውጣት ወይም ሰፉን መስበር ማለት ጩቡ መስራት ማለት ነው፡፡ ጩቡ መስራት ደግሞ ከባህል ከእምነትና ከህብረተሰብ ውጭ መሆን ስለሆነ ሀራሙና ጫጳና ያደርጋል፡፡ ይህም ሰፉን ከግለሰብ እሰከ ቤተሰብ ከቤተሰብ እስከ ህብረተሰብ ተቀባይነት እንዲኖረውና ማንም ሰው አክብሮ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ጥፋተኛ የሆነ ሰው በጠፋቱ ምክንያት የትኛውም ውሳኔ ቢተላለፍበት እንኳ ያለ አንዳች ጥበቃ ተቀምጦ ፍርዱ እስኪፈፀምበት ድረስ ይጠበቃል እንጅ ወዴትም አይሸሽም፡፡ ስለዚ የህዝቡን ባህልና ወግ ጠብቆና አክብሮ መኖር ከሁሉም የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

ሰፋ ተፈጥሮአዊ ሲሆን ብዙ አይነት ሰፋ ሊኖር ይችላል (ወደ ብዙ ይከፈላል)፡፡ ከነዚም የውሃ፣ የምድር የተፈጥሮ፣ የእንስሳት፣ የአራዊት፣ የቤተሰብ፣ የልጆች፣ የእግዳ፣ የአንጋፋ፣ የገደኛ፣ የጎረቤት፣ የሀገርና ሌሎችም ይኖራሉ፡፡ በተለየ ሁኔታ ግን ሀብት ያጣ አደጋ ያጋጠመውና የታመመ እንዲሁም እርግማን የደረሰበት (የመጣበት) ሁሉ መርዳትና መደገፍ የህብረተሰባዊ ሰፉ ነው፡፡ ይህ ሁንታ ዛሬም ድረስ በቦረና ኦሮሞ ዘንድ የ-- እና-- ስነ-ስርዓት ያለና የሚታወቅ ነው፡፡

እናቶችም መጠበቅ ያለባቸው ሰፉ ሲኖር ሴት ልጆቻቸውን ስለ ቤት አያያዝ ስለ ልጅ አስተዳደግ ስለ ባል አያያዝ ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡



ስእል 2: ሴቶች በባህላዊ ልብስ በሲቄ ስርአት

ሌላው የሰፉ መርህ ደግሞ ሁሉም ሰው ጋር ክብደት ያላቸውና የሚከበሩትን ማወቅና ማክበር ነው፡፡ ለምሳል ሰማይ ምድር ተራራ ዉሀ አባት እናት ታላቅ የመሳሰሉት ክብር መሆኑን ማወቅና ማክበር ነው፡፡

## 1.2 ባህል

ባህል የአንድ ሀገር፣ አካባቢ ወይም ማህበረሰብ የማህበረሰብ መገለጫ ነፀብራቅ ሲሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈና እየተወራረሰ የሚሄድ እሴትዊ ሀብት ነው፡፡

የባህል ዋነኛው ምንጭ የህዝቡ አኗኗር፣ ዕምነት፣ ዘ-ልማድ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሀብት፣ የተፈጥሮ፣ የእንስሳትንና እጽዋት አያያዝ፣ የቤተሰብና የጎረቤት ሁኔታ፣ የመሬት አቀማመጥ የአፈርና የአየር ንብረት (ደጋ፣ ወይናደጋ፣ ቆላ)፣ የህዝቡ አመለካከትና እይታ፣ ንቃተ ህሊና፣ የስራ ባህልና ተነሣሽነት፣ የማህበረሰቡ አስተምሮት፣ በአካካቢው የሚገኝ እንስሳትና አራዊት፣ የተክልና የሠብል አይነቶች፣ የተፈጥሮ ሀብት (ማዕድን፣ ነዳጅ፣ ለም መሬትና፣ ውሃ)፣ የመሳሰሉት ሲሆኑ

ይህም ለህዝቡ አብሮ መኖር፣ መፈቃቀድንና መተሳሰብን ትልቅ አስተዋጹኦ ያበረክታል፡፡ ከዚህም በመነሳት የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የአዘፋፈን፣ የመጠለያ አሰራር፣ የቤትና የውጪ መገልገያ መሳርያዎች አሰራር፣ የፀጉር አበጣጠርና አሰራር፣ ጨዋታና መዝናኛ፣ እንዲሁም የጋብቻ፣ የሀዘን፣ የቀብር፣ የበአላት አከባበር እና ሌሎች መሰል የማህበረሰቡ እሴታዊ መገለጫዎች ይገነባሉ፡፡

ባህል የአንድ ሠው አልያም የአንድ ትውልድ ሀብት ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡ ዘመን ተሻጋሪ የጋራ እሴታዊ ጸጋ ሲሆን ከትውልድ ትውልድ በመወራረሰ እየዳበረና እየጎለበተ ይሄዳል፡፡ ማንም ሰው ባህልን ተቀብሎ በማቀበልና ወርሶ በማውረስ ትውልድን በእውቀትና በስነምግባር ማነጽ ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ አካታ ለሀገር ምሰሶ የሚሆኑ ባለፀጋ ትውልድንና ማህበረሰብ ማበርከት ይቻላል፡፡ አልያ ግን ማህበረሰቡ የኖረበትን ባህል በመተው በማያውቁት /በባእዳን/ ባህል ተዘፍቆ እድገት ለማምጣት መዳከር አሳን በዛፍ መውጣት እንደመፈተን ከባድ ሲሆንበት ውጤቱም የበጎ ፈቃደኛ ድኩማንና መፍጠር የማይችል ትውልድ እንደመስራት ይሆናል፡፡ የእንዲህ አይነት ሁኖች ኪሳራ ባታላ ባይ-ታኢም በቆይታ መ-ታ-ኤ-ቱ አይቀርም፡፡ እኛም ለዚህ ጣባ-ሀቃ የምንሆነው የጠፋንበትን የኩሽ ስልጣኔ በማስታወስ ነው፡፡

የፈለግነውን ያህል እንወቅ ምጡቅ አይምሮ የተቸረው ሣይንቲስትም እንሁን፣ አልያም ልብስ ያልበሡትን ማህበረሰብም ብንሆን ሁሉም ነገር ከውሀና ከአፈር መሠራቱን ረቢ የሰጠን እውቀት ይነግረናል፡፡ የገዳ ሀዩዎች ስለዚህ ጉዳይ ሲናገሩም፣ አፈርና ውሀ ያለው ህዝብ አይራብም ይላሉ፣ ሲቀጥሉም ረቢ የመረቀው ህዝብ ደግሞ አፈርና ውሀ ላይ ዝናብም ይሰጠዋል ይላሉ፡፡

ነገር ግን ትልቁ ቁም ነገር ያለው ደግሞ እንዴት እንዴት እንደሚሆን ማወቅ ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ እውቀት ሁለት አይነት አለው ይላሉ የገዳ ሀዩዎች፡

1. የፋልፋላ እውቀት እና
2. የዋቃ እውቀት ነው፡፡

የፋልፋላ እውቀት ማለት አንድ ሰው ትልቅ እውቀት ኖሮት ባለው እውቀት ሀገር የሚያፈርስ ሰውነን የሚያጠፋ ተግባር የሚፈጽም ሲሆን ሲሆን የዋቃ እውቀት ደግሞ አንድ ሰው ባለው ትልቅ እውቀት ሀገር የሚገነባ ህዝቡን የሚያሻግርና ከሮሮም የሚጠብቅና ዋቃ የሚወደውን ሁሉ የሚሰራ ነው፡፡ ስለዚህ በኢኮኖሚ ያደገ ማህበረሠብ፤ በእድገት ላይ ያለ እንዲሁም ኋላቀር የሚባለው ሁሉ ከባህል ጋር አብሮ ያድጋል እንጂ አይጠቅምም ተብሎ ጥለውት የሚሄዱ ነገር የላቸውም፡፡ የትኛውም እውቀት ከባህል ውስጥ ስለሚመነጭ ባህሉን ጠንቅቆ የሚያውቅ አካባቢውን ለመረዳት አይቸገርም፡፡ አካባቢውን የሚረዳ ደግሞ ችግር መፍቻ ቁልፍ ሲኖረው እክልንም ሲያጋጥመው በቀላሉ የሻገረዋል፡፡ ላወቀበትና መጠቀም ለቻለ ህዝብ፤ ባህል የእውቀት ባህር ሲሆን የባለጸጋነትም በር ነው፡፡ ስለዚህ ባለፀጋ መሆን የሚሻ ማህበረሰብ ካለ ባህሉን ጠንቅቆ ይወቅ አልፈውም ባህሉን ይመርምር ይኑረውም፤ እርግጥ መሠጠት ቢጠይቅም ቀለሉ፡፡

እንግዲ የኦሮሞ ህዝብ ባህሉን ለረጅም ዘመናት ሲኖርበት በውስጡም ያለውን እውቀት እየፈለፈለ በመጠቀም ነው፡፡ በህይወቱ ውስጥም በመተግበር ጥቅምና ጉዳቱን ለይቶ በመረዳት ሲጠቀምበት የኖረ ሲሆን ከዚህ በመነሳት ኤባ እና ሀራሙን መከሰቻ ስሌቶቹነንም በተጨባጭ ስለሚያውቁት ውጤቱን ከወዲው የሚነግሩን ምን እንደሚከሰት ስለሚያውቁት ነው፡፡ ነገር ግን ዛሬ በብዙ ህዝብ ዘንድ ያ ሁሉ እውቀቶች በተለያዩ ጊዜያት በነበሩት ጫናዎች እየተጎዳና እየተጎሳቆለ ይምጣ አንጂ

አያሌ እውቀቶችን አቅፈው ያቆዩም ደጋጋዎች አልታጡም፡፡ ይህ እውቀት ለወደፊት በጥልቀት ቢጠና ለሀገራችን ሁለንተናዊ መሰረት ሆኖ ሊያገለግል የሚችል የሳይንስና ፈጠራ መፍለቂያ እንደሚሆን እሙን ነው፡፡ ገና ያልተዳሰሰና ተቀብሮ የተረሱ አያሌ እውቀቶችን በተገቢው ለመጠቀም በጥናትና ምርምር መደገፍ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ይህ ቱባ ባህልና የህይወት ፍልፍና በጥልቀት የመጠናቱ ምክንያትም ለነገው ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለሳየይንሳዊ ፈጠራዎች እርሾ ሆኖ የሚያገለግሉ አያሌ የእውቀት መሰረቶችን በውስጡ አቅፎ ይገኛል፡፡ የዚህ ትውልድም ሀላፊነትም የተረሳውን አጥንቶ ያለውን ደግሞ አጥርቶ በመንከባከብ በመጠቀምና ለመጪው ትውልድም ማውረስ ትውልዱ መወጣት የሚኖርበት እና የሚጠበቅበት ሀገራዊ ግዴታ ነው፡፡ ይሁንና የሚያውቁትን በመተው የማያውቁትን በመከተል (መሆን መሞከር) ለማህበራዊ ችግርና ህብረተሠባዊ ልዩነትን በማምጣት በማህበረሰቡ መካከል የተዛባ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ለአብነት ያህልም የምስራቁን አለም የንጉሳዊ ቤተሰብ ስርአት በመከተል የዲሞክራሲያዊ ስርአትንና የህዝቦች እኩልነትን በመፍጠር ለረጅም ጊዜ ሲተዳደርበት የነበረውን የህዝብ ስራአት በመስበር በህዝብና በመሪ መካከል የተዛባ ግንኙነት (ከሌው የበላይ ነኝ የሚል ፊውዳላዊ ስርአት) ፈጥራል፡፡ እናንተን እንድንገዛም ፈጣሪ ፈቅዶልናል ሾሞናል በማለት በነሱና በህዝቦች መካከል የተዛባ የማህበራዊ ግንኙነት እንዲኖር አድርገዋል፡፡ የሚያሳዝነው ነገር ግን እነኚ የቤተሰብና የዘመድ ስብስብ አባላት የህዝብን እጣ ፈንታ ሰፉን በማያውቁና የዋቃን ሴራ በሚያጣምሙ ሀራሙዎች እጅ በመጣል ጋቱማ በህዝቡ ላይ አምጥተዋል፡፡ ይህ ሁኔታም ሀገራችንን ከምእተ አመታት በፊት የገጠማት ቢሆንም እስከ አሁንም ተሰባብሮ ያላለቀና ከዛ አስተሳሰብ ያልወጡት ጥቂቶች እንደሚኖሩ እሙን ነው፡፡

### 1.2.1 የጋብቻ ሥነ-ሥራአት

የየኦሮሞ ህዝብ ሴራ ሲኮ-ማንዶ በመከተል ሚስት ያገባሉ፡፡ ይህ ሴራ ጂላ አባ ቦኩ ኦዳ ሮባ ጊኒር በሚገኘው የተደነገገውን፡፡ በ ወላሼ ሆራ ቦቃ ለህዝብ የተነገረ አዋጅ ነው፡፡ ይህ ሰፉና ሴራ በመከተል መቷል ስለዚህም ጋብቻቸው የተሳካ ነበር፡፡ አስቲ ይህንን የጋብቻ ፍልስፍና በጥቂት እንቋደስ፡፡

### 1.2.3 ያለ ምክር ያገቧት ያለምክክር ይፈቷቷል

የዚህ ፍልስፍና ትርጉሙም ሚስት የጎሣ ቤተሰብ አንጋፋና ጎሳ ሣይማከር ያገቧት ቤተሰብ አንጋፋ ሣይማከር ትታ ትወጣለች ማለት ነው፡፡ ያለ ጎሳ እና ታላቅ ምክር ያገባች ሰተ ያለ ጎሳ /ታላቅ 2 ወቅተ ትወጣለች ባሉን ትሂዳለች፡፡ አንዲት ሴተ ወንም ሚሰረት ብታገባ የራሷን ቤተሰቦች ትታ ከዚያን ቀነ ጀምራ ወደ ባሏ ቤተሰቦቸ ትቀላቀላለች የሱ ጎሳ አባልም ትሆናለች፡፡ በዚህም ምክኒያት ልጆ[illegible]ንም ስለ ባሏ ጎሳዎቸ ስታሰተምር ታሳድጋለቸ ሆኖም ወደ ባሏ ቤተሰቦቸ በጣም እየቀረበቸ አንድትሄ ያደርጋታል ፡፡በሌላ መልኩ ሴት ልጅ የአባ[illegible]ን ንበረት አትወርስም የባለሏን ንብረተ ትወረሳለቸ እነጂ፡፡ ሚስት ከባለሏ ጋር ከተጣላች ወደ በተሰቦ[illegible] ሳይሆን ወደ ባሏ ታላቅ ወንድም በመሄድ በደሉን ሁሉ ለርሱ ትናገራለች እሱም ወንድሙን ተቆጥቶ ያሰታርቃታል ሲያታረቅም ለሷ በማገዝ እሱን ይገስፃል፡፡ አርሲ የአንድ አካባቢ ወንድም አብሮ አደግ አያጋቡም ይናናቃሉ ይላሉ፡፡ ስለዚህም ዋቤ ማዶ በመሄድ ሚስት ሲያጋቡ ጋብቻውም ሲኮ ወንደ ወንዱ ለሲኮ እንዲሁም የአንድ አካባቢ ልጆቸ መጋባት በቤተሰብ መሃል የኢኮሮሚ ፍላጎት ግጭት ሲነሳ ትዳር እንዳይፈርስም ጭምር ይጠቅማል ይላሉ፡፡



ስእል 3፡ የሙሽራዋ ሚንጃች

በተጨማሪም ልጆትና ልጁ ሰባት አባታቸውን ቆጥረው አንድ ጎሳ አባል አለመሆናቸው በሽማገሌ ተረጋገጦ ነው ጋቢቻ የሚፈፀመው፡፡ አረቲሰት ቀመር የሱፍ በአንድ (አሾ … አሺላ) ዘፈኑ ውሰጥ የሲኮ ማንዶ ጋብቻ ለማሰታወስ አጢነልዋል፡፡

### 1.2.4 ሶዳ /አማች/

የልጁ አባትና የልጅታ አባት (MOIETY) በኦሮሞ እና ስጋ በዎሮኛ የ ሲሆን ዝምድናው የሚፈጥረው በጣም ትልቅ ክብረ ለራስ አላቾ በሁለት መካክ የጎሳ ልዩነት ስላለ ክብር አላቸው፡፡ የራስና ሶዳ በራስ መጠጋት እንደ ሰሎን አ..ር ይሆናል፡፡ ልክ ሰሎን ፊት-ለፊት ያል አ..ር ሰው ሲመላለስ አንዴ መረገጡ አይቀርምና፡፡ ስለዝህም ከላይ ማራቅ አስፈላጊ ግዴታመ ነው መጠጋጋቱ አሁን አሁን መገናኘት ለመጣላት መንገድ ይከፍታል፡፡ ከጋብቻ በኋላ ሆነ ከጋብቻ በፊት ሁለቱ ሶዳ ከቁጥጥር ውጭ ሆነ ግኑኝነት እንዲኖራቸው አይደረግም አይፈለግም፡፡

### 1.2.5 ሶዳና እሳት ከሩቅ

እሳተና ሶዳ ከሩቁ መሞቅ እሳትን መተው አይቻልም ማቀፍም አየቻልም ሶዳም ልክ እንደዛው ከሩቅ ነው መዋደድ ይላሉ፡፡

አንድ ሰው እራሱን ጥሎ ሶዳ ጋር መግባት የለበትም በመሀላቸውም መስመር ሊኖር ይገባል፡፡ እንድሁም ሁለት ሶዳዎች መጣላት የለባቸውም ይህና ሌሎች መሰል ሕጎች ጊኒር በሚገኘው ኦዳ ተደንግጎ በወላሼ በሆነ በቃ ለህዝቡ ታውጆ ነበር በጊዜው፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ትዳሮች ረጅም አመት ይዘልቁ ነበር፡፡ የአሁኑስ እንዴት ነው እንደሆነ ለናንተ ለአንባቢሆች ትቻለው፡፡



ስዕል 4: የሙሽሪት የሸኝት ጊዜ

## 1.2 የምስጋና እና  የልመና በአል (ኢሬቻ /ኢሬሳ/)

እሬቻ /እሬሳ/ ብዙ ትርጉም ያለው ሲሆን፤

- በእርቅና በበአል ቀን በእጅ የሚያዝ እርጥብ የሮሙቆርሳ ሳር እሬሳ ይባላል፤
- ሰዉነት የሚያሹ አያንቱ ጋር ሂደው ከታሹ በዋላ የሚሰጥ ስጦታም እሬሳ ይባላል፤
- እሬሱ ማለት አንጌሱ (ማ-አንገስ) ማለት ነው፡፡

በአንድነት በመሆን ካዳናና ጋእና ለማቅረብ የሚከበር በአልም እሬሳ ሲባል በአሉም በአመት ሁለቴ ይከበራል፡፡ ኢሬሳ ቱሉ በአርፋሳ ወር የሚከበር ሲሆን ሠዎች በአንድነት ወደ ተራራ

በመውጣትያልተቀጠቀጠና አካሉ ያልጎደለ ኮርማ መስዋት በማቅረብ ረቢን የሚለምኑበት በአል ነው፡፡

ሁለተኛዉ ኢሬሳ ሆራ (መልካ) ደግሞ የክረምት ዝናብ አልፎ እሸት መቀመስ በሚጀምርበት በመስከረም ወር በአንድነት ወደ መልካ በመሄድ በእሬቻ ቱሉ የለመኑት /የጠየቁት/ ስለደረሰላቸው ሚሲ-ጋአና ለማቅረብ የሚከበር በአል ነው፡፡

### 1.3 የጎረምሳ ልጆች በአል (ታቦሬ)

አያና ታቦሬ (ኡኬ) የወጣት ወንዶች በአል ሲሆን ጋሜዎች 16 ዓመት ሲሞላቸውና ወደ ፎሌ መሻገራቸውን ለማብሰር የሚያከብሩት በአል ነው፡፡ በአሉም በክረምት ወር ሲከበር ልጆቹም በጩካ ጎጆ ይሰራሉ፡፡ በበአሉ ላይም የልጁ እናት ዘጠኝ (9) ቢጢሌና እርጎ በማቅረብ በልጃ ጉልበት ላይ በማኖር ትመርቀዋለች፡፡ ሌሎች ልጆችም በጎጃ ውስጥ በመሆን የተዘጋጀውን ሁሉ ከመቀደሱ በዋላ የተመረቀው ልጅ ጎጆውን ሰብሮ ይወጣል፡፡ ልጆቹም ለምን ጎጆአችንን አፈረስክ ብለው በጩካ ልምጭ ለመምታት ሲያሳድዱት እሱም እያቅራራ ያመልጣቸዋል፡፡

በኋላም ወደ ድሬ (ሜዳ) በመውጣት ቃጩ (ጅራፍ) በማጮህና ትግል በመጫወት ቀነን በደስታ አብረዉ ያሣልፋሉ፡፡ ዛሬ ዛሬ የዚህ በአል አከባበር በየአካባቢው የተወሰነ ልዩነት ሲኖረዉ አሁን አሁን በአንዳንድ አካባቢ በተለያየ ሁኔታ ይከበራል፡፡ ጋሜ ኡኬ ወጣ ማለት ከልጅነት ወጣ እንደ ማለት ሲሆን ከዛ ቀን ጀምሮ ከልጆች መኘታ በመውጣት ከብቶችን ከአውሬ እየጠበቀ ከታላላቆቹ ጋር ያድራላል፡፡

### 1.4 የልጃ-ገረዶች ልጆች በአል(ኢንጊጫ)

አያና እንግጫ የልጃገረዶች (ያላገቡ ሴቶች) በአል ሲሆን የቁኒ በአል በመባልም ይታወቃል፡፡ ይህ በአል በአመት አንዴ የሚከበር ሲሆን ሴቶች በአንድነት በመሆን የሚከበር በአል

ነው፡፡ የበአሉ አከባበርም በጃላቡልቲ አያና ሴቶች በቡድን በቡድን በመሆን አምረውና ደምቀው እየዘፈኑ ወደ ወንዝ በመውረድ የቁኒ ሳር ይነቅሉና እየዘፈኑ ይመለሳሉ፡፡ በዚያዉ ቀን ማታ ያመጡትን ቁኒ ባቴ ይጎነጉኑታል፡፡ የተጎነጎነው ቁኒ እንግጫ ሲባል በሚቀጥለዉ ቀን ጠዋት እየዘፈኑ እንግጫውን በሰፈራቸው ሰዎች ማን-ዱሬ ላይ ያስራሉ፡፡ በዚህም ጊዜ ምግብ ይሰጣቸዋል ይመረቃሉ ቅቤም ይቀበላሉ፡፡ በመጨረሻም ሁሉም በቡድን የነበሩት በአንድ ቤት በመገናኘት እየዘፈኑ በአሉን በማክበር ቀኑን ያሳልፋሉ፡፡

### 1.11 እህል መድረሻ ጊዜ በአል (ጋኒ)

አያና ጋኒ የቂሌ በአል በመባል ሲታወቅ በባአሉ ቀን የከብት በረት ውስጥ ገንፎ በማገንፋት ከብቶች እንዲረቡላቸው ይመርቃሉ፡፡ ቀኑንም የቂሌ ጨዋታ እና ፈረስ ጉግስ በመሽቀዳደም ሲያሳልፉ ለበአሉም ልዩ ድምቀት ይሰጠዋል፡፡ አሁን አሁን ይህ በአል በአንዳንድ አካባቢ በተለያየ ሁኔታ ይከበራል፡፡ ከነዚህም በአላት በተጨማሪ ሌሎች የሚከበሩ በአላት ሲኖሩ ከነዚህም፡

- አያና ናቢ - የወጣቶች በአል፤
- አያና አብዳሪ - ምድር ምርት እንድትሰጥ (ዘር እንድታበቅል) ለመለመን የሚከበር በአል፤
- አያና ጃሪ - የሰላም በአል ሲሆን በዚህም ቀን ዋቃ ለሰዎችና ለከብቶች በሰላም እንዲጠብቃቸው ለመለመን የሚከበር በአል ተጠቃሽ ናቸው፡

# ትምህርት 2

## የገዳ እርከንና አደናር

ገዳ ከኩሽ ህዝቦች የኦሮሞ እሴትና ፍልስፍና ሲሆን የተለያዩ ስርአቶችን በውስጡ አቅፎ ይገኛል፡፡ በዝህ አካታ አውቆ በማሳወቅ ተግባብት በአንድነትና በአብሮነት በሺዎች ለሚቆጠሩ አመታት ቆይታል አሁንም እየኖረ ይገኛል፡፡

የገዳ እርከን ማህበራዊ አገልግሎትንና ጠቀሜታን ማእከል በማድረግ የስራ ሀላፊነትና ተጠያቂነትን ለህዝቦች በመስጠት የተዋቀረ ነው፡፡ ይህም በሁለት መልኩ ይመሰረታል፡፡ ይህም አንደኛው አባቶቻቸው ከ40 ዓመት በታች የሆኑት እንደ ተወለዱ የመጀመሪያው ገዳ እርከን ይገባሉ፡፡ ይህም ማለት አባቱ ስልጣን ላይ እያለ የተወለደ ልጅ ዳባሌ ይገባል፡፡ ይህ ከ40 አመት በኋላ አባ ገዳ የመሆን እድል ያለው ይሆናል፡፡ ሌላው የጃርሳ ልጆች በትውልድ እድሜ እኩል ሳይሆኑ በአንድ ገዳ እርከን ውስጥ የሚገኝ ማለት ነው፡፡ ይህም አባቶቻቸው ከገዳ የወጡ ልጆች ማለት ነው ወይንም ፡፡ ይህም እንተወለዱ የሚገቡት እርከናቸው ደግሞ ሌላ እርከን ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት ከ40 አመት ቀድመው ገዳ ይገባሉ ወይንም ዘግይተው ከገዳ ይወታሉ በዚህ ምክንያት አባ ገዳ የመሆን እድል ሊያጡ ይችላሉ፡፡ የማህበራዊና የስራ ድርሻ እንደየእድሜ ያቸው ተመሣሣይ ሲሆን የስላጣን ተጠያቂነታቸው ላይ ልዩነት ይኖራቸዋል፡፡ በአጠቃለላይ ስም የእርከን ስሞች እንደሚታወቀው ይከተላሉ፡

1. ደበሌ ከ0---8
2. ጋሜ ከ9-16
3. ፎሌ ከ17-24
4. ራባ ከ25-32
5. ዶሪ ከ33-40
6. ገዳ ከ41 48

7. ዩባ 1 ከ49-56
8. ዩባ 2 ከ57-64
9. ዩባ 3 ከ55-72
10. ዩባ 4 ከ73-80
11. ገዳሞጂ ከ80 በላይ

### 2.1. ደበሌ

ደበሌ ወይንም ደበሎማ የመጀመያው የገዳ እርከን ሲሆን ወንድ ልጅ እንደተወለደ የሚገባበት እርከን ነው፡፡ ይህ ደረጃ ህጻናት ዕድሜያቸው ስምንት (08) አመት እስኪሞላቸው የሚቆዩበት የገዳ እርከን ነው፡፡




ስእል 5፡ ዳባሌ

ይህ እርከን አባቶቻቸው በገዳ ስልጣን ላይ የሚገኙ ልጆች የሚያዝ ነው፡፡ ደበሌ የልጅነት እርከን እንደመሆኑ መጠን በዚህ ደረጃ ያሉ ልጆች በፀጉራቸውም ይለያሉ፡፡ የደበሌ ፀጉር አይላጭም ጉዱሩ ያሳድጋል እንጅ፡፡

ደበሌ ይህንን እርከን ሾልኮ እስኪያልፍ ድረስ ስም አይወጣለትም በቤት ስም (እንደነ ፉኜ ጃልዴሶ ዶጮ) ይጠራል፡፡ በዚህ ዕድሜ ላይ ያሉ ልጆች ቤተሰባቸው የወተት ላም ከሌላቸው ጎሳ ወተት ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ደረጃ ልጆች የተወሰነ የስራ ድርሻ ስለሌላቸው በሰፈር ውስጥበእናታቸው ስር በመሆን በእንክብካቤ

ያድጋሉ፡፡ መሰረታዊ የሆነ የሰፉ ህግንም ጥሩና መጥፎን መለየት ይማራሉ፡፡ በተጨማሪም በአያቶቻቸውና ቅድማያቶቻቸው ተረትና ሂቦ ይነገራቸቃል፡፡

## 2.2 ጋሜ

ጋሜ ሁለተኛው የገዳ እርከን ሲሆን በአንዳንድ ቦታ ጋሜ - ጢጢቆ ወይም ኢቲማኦ ይባላሉ፡፡ ልጆች የደበሌን እርከን ጨርሰው በቀጣይ የሚያልፉትበት የእርከን ደረጃ ሲሆን እድሜያቸውም ከ8-16 ነው፡፡የደበሌ እርከንን የጨረሰ ልጅ ጉዱፉውን ተላጨወቶ ቤተዘመድ ተጠርቶ የአንድ ጎሮምሳ ከብት ስጦታ ከተበረከተለት በኋላ ወደ ጋሜ የእርከን ደረጃ ይሸጋገራል፡፡ በዚህ ደረጃም በህመቿሳ ስም ይወጣለታል፡፡ ከዛቀን አንስቶ የቤት ስሙ ይቀርና በህመቿሳው ስም ይጠራል ይታወቃል፡፡




ስእል 6፡ ጋሜ

ጋሜ የፀጉር አቆራረጥ ልዩ ያደርገዋል፡፡ ወደዚህ እርከን የገቡ ልጆች ከአራት (4) አመት በኋል ጋሜ ተላጭተው ሮጌ (ጆንትራ) በማበጠር ጥጃ ይጠብቃሉ ውሃ ይዋኛሉ ፈረስ ግልቢያ ይለማመዳሉ፡፡ በተጨማሪም እርሻ እስፖርታዊ ውድድር ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም መብትና ግዴታን ስለ ፖለቲካና

አስተዳደር ህግና ደንብ ህበረተሳቦዊ አገልግሎት ህብረተሰባዊነት፡፡ ሴቶችም ጥጥ መፍተል ልጅ አያያዝ አስተዳደግ ቤት አያየዝ የጎተራ እህል አያየዝ ምግብ አሰራራ የመድኒት ቅጠል መለየት ልጆችን መኝከባከበ ይለምዳሉ፡፡ ጋሜ ብዙ ስራ ይኑረው እንጅ በዚህ ደረጃ ላይ ከቤተሰብ ቁጥጥር ውጭ ሳይሆን እርስ በእርስ ይጫወታልሉ ይቀራረባሉ መቀራረብ ይጀምራሉ፡፡

## 2.3 ፎሌ

ፎሌ አንዳንድ ቦታ ጋሜ ጉጉዳ ይባላል ይህም ጋሜ ጢጢቆ ኡኬ ውስጥ በማለፍ ወደዚህ እርከን ይሻገራል፡፡ የታቦርሬ በዓል የልጆች የኡኬ በዓል ከተከበረ በኋላ የሚያልፍበት እርከን ነው ፎሌ፡፡ በታቦሬ ቀን ልጆች ከጋደኞቻቸውና ከወንድሞቻቸው ጋር ቢጢሌ እየበሉ ወተት እየተጡ በዘፈንና በደስታ ያከብራሉ፡፡ በዚህ ቀን ጎጶ ተሠርቶ በጎጶ ውስጥ የልጅየው እናት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ በሚሟላት በልጁ በእግሩ ላይ በማድረግ ዘጠኝ ቢጢሌ በመስበር (በመቁረጥ) የእርጎ ወተት በመደባለቅ በመጨመር ካዘጋጁ በኋላ ጓደኞች እና ወንድሞች በተገኙበት መርቃ ይህንን በአል በዘፈን ይጀምራሉ፡፡ በዚህም መሀል ልጁ ጎጆ ሰብሮ ሲወጣ ልጆቹም ለምን ጎጆአችንን ሰበርክ ብለው ጨካ ይዘው ያባርሩታል እርሱም እያቅራራ ያመልጣቸዋል፡፡

ይህ የሚያሳየው ከልጅነት መውጣቱን ሲሆን ከቤት ወጥቶ ቤት ስር ተኝቶ ከከብት አብሮት እንዳይበላ ይጠብቃል፡፡ጎጆ የወጣ ልጅ ቢራ ላይ ገፍቶ ይጨፍራል ከብትም ይሸለማል፡፡




ስእል 7፡ ፎሌ

የኡኬ በዓል ክረምት ላይ ሲከበር ኡኬ የወጣ ልጅ መስቀል ላይ ጊፍቶ ጠፍሮ ከብት ይወስዳል በዚያው ፎሊሚ መጨፈር ይቀጥላል፡፡ ከቤት ወጥቶም ቤት ስር ተኝቶ ከብት አብሮት እንዳይበላ ይጠብቃል፤፤ በተፈጥሮ ሁኔታም ስናይ ልጆች እስራ ስድስት አመት ሲሞላቸው ይጎረምሳሉ ባህሪያቸው ከልጅነት ይለያል ድምጽ ይጎረንናል፡፡ በዚህ ልክ ሀላፊነትና ተጠያቂነታቸውም ይቀየራል፡፡

በፎሌ እርከን ያሉት ወጣቶች አደን ያድናሉ ከከቢቶች ላይ አራዊት ይጠብቃሉ ፈረስ ይጋልባሉ ትግል ይጫወታሉ እርሻ ማረስና አባታቸውን ማገዝ ይጀምራሉ፡፡ ከጓደኞችና ሌሎች አካባቢ እኩያ ጋር ይበልጥ ይተዋወቃሉ ይቀራረባሉ፡፡የፎሌ ሌላኛው ተግባር የቡታ ኮርማ መጣል ነው፡፡ ይህም ቡታ ሲታደረድ ፎሌ ነው የሚጥለው፡፡ ፎሌ የቡታን ስጋ ከጣለ አንድን ታፋ የሰጠውተሸምቶ እየበጣጠሰ ይበላል አንዱ ለሌላው ጉልበቱን የመሻማት አቃቱን ያሳያል ያስመሰክራል እንዳንበሳ እየተቃማ እየበጣጠሰ ይበላል ቡታ ከተጣመመ ፎሌ ኮርማ አጣጥሞ ለማለት መብት አለው፡፡ ያለ ፎሌ እንጅ ደግሞ ቡታ አይታረድም ስጋውን አልበላም ማለት ይቻላል፡፡ አባገዳው ህግና ወግን ካጣመመ ፎሌ አባገዳውን ይዘልፉል እንዲሁም አባገዳ

ጠንካራ ከሆነ ያሞግሳሉ ዘፈናቸው ውስጥ ተው ይባላል እንጅ አይቀጣም ፎሌ፡፡

ፎሌ ሀገሩን ሆነ እርስ በእርስ መተዋወቅ ይጠበቅበታል ገዳንም በጣም እያጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ በራሳቸው በመምረጥ ሀዩ ሂሪያ የሚባል ስድስት አባላትን ያለው ኮሬ ያዋቅራሉ፡፡ ፎሌ መሀልም የተለያዩ እስፖርታዊ ውድድሮች አሉ ፈረስ ግልቢያ ነፃ ትግል አደን ሩጫ እና ሌሎች ትግሎች ፎሌዎች ብዙውን ጊዜ አብረው ስለሚውሉ አብረው ይሠራሉ በይበልጥ ይተዋወቃሉ ይግባባሉ፡፡ ድሮ ድሮ ፎሌ ቢገድል አይጠየቅም ቢሞት የህግ ጉማ አይወጣለትም ይባላል፡፡

ወጣቶች በዚህ እድሜ ከቤተሰቦቻቸው ነፃ ወጥተው እየወጡ ይሄዳሉ እንዲሁም ከቤተሰብ እየራቁ የሚሄዱበት ጊዜ ነው ፎሌ የሚጓዝበት ዕድሜ ነው ፎሌ እንዲሁም ይህ ጊዜ ጥንካሬውን እውቀቱንና ጀግንነቱን ማሳየት የሚጀምርበት ነው፡፡ ለህብረተሰቡ ትርፋማ ስራ የሚሰራበት ከብቶችን ይዞ ደረባ እና ሆራ የሞሄድበት ከጎረቤት ጋር ርቆ የሚሄድበትና ከከብቶች ላይ አራዊትን የሚከለክል እና ቤተሰብን የሚጠብቅቅበት እድሜ ነው ፎሌ፡፡ ከወገን ላይም ሮሮ ይከለክላል፡፡

## 2.4 ራባ

ራባ እድሜያቸው ከ24-32 አመት የሚገኙ ወጣት ወንዶች ሲሆኑ አንዳንድ ቦታ ቆንዳላ ይባላሉ፡፡ የራባነት ደረጃ ወጣቶች ከፎሌ በመቀጠል የሚያልፉበት የገዳ እርከን ሲሆን በጡንቻና በጥንካሬም ይበልጥ የሚፈረጥሙበት እድሜ ነው፡፡ በዛው ልክም ሀላፊነታቸውና ተጠያቂነታቸውም ከፍ እያለ ይሄዳል፡፡ ራባች ብዙ ሀላፊነታቸው የቤተሰቦቻቸውን ጫንቃ ማሳረፍና ወገንን ከጦርነት፤ ከሮሮና አስከፊ ነገሮች መመከትነው፡፡ አባት ልጁ ራባ ሲሆንለት ልጄ ደረሰልኝ ቀዬ ያቀናልኛል ብሎ መተማመኑ ይገዝፍለታል፡፡ ልጁም የአባቱን ስም ያስጠራል የአባቱን ተግባራትና የሚበልጥ ስራዎችን ሲከውን ለሠርግና

ለአስተዳደርም የሚታጨው በዚሁ እድሜ ነው፡፡ በዚህም እርከን ላይ ያሉ ወጣቶች ትልቅ ገልማ ከተሰራ ነጭና ቀይ ምልክት ያለው ነገር ያቆማሉ፡፡ በሀላ ይህንን ገሬ የሚመራ ከራሳቸው ይመርጡና ወደ ተሰራው ገልማ ይገባሉ፡፡

አባቶቻቸው ደግሞ ጫካ ሄደው የሚኤሳ እንጨት ቅርንጫፍ ይዘው ይመለሳሉ በጡኔ እና በመኬ ዘፈን የልጃቸውን እናት እያደነቁ ቅጠሉንም የውጭ በር ላይ ይሰካሉ፡፡ በዚን ጊዜ የልጆቹ እናቶች ወተትና ውሃ ደባልቀው በገበቴ ካቀረቡ በሀላ የልጆቻቸውን ፀጉር አርሰውበት ይላጫሉ፡፡ ከዛ ጨሌ በማድረግ ካሳመራቸው በሀላ የምትታለብ ላም ከነልጆችዋ ይሸልማቿል፡፡ እናቶችም እዚህው ምግብ ያመጡላቸዋል ከልጆቻቸው ጋርም አይገናኙም ምግብ ሲሰጡም የልጁን ስም ሳይሆን የጎሳውን ስም ነው የሚጠሩት፡፡ ወጣቶቹም ከጋደኞቻቻቸው ጋር ለሁለት ሳምንት ከቆዩ በሓላ ባህላዊ ልብስና ትንሽ ሉጮ የታሰረበት ቦኩ ይዘው ከኡልማ ይወጣሉ፡፡ የተሸለሙትንም ከብቶች ወደ ቤተሰባቸው ከብት ቀላቅለው ይንከባከባሉ፡፡ በአሉም ይህ በአል የጎዲያ በአል ሲባል ድግስ ተደግሶ ይጨፈራል ከዚ በሀላ ኡለማ ወጡ የባላል፡፡ በመቀጠልም እነዚህ ወጣቶች ለስምንት አመታትም አብረው ይቆያሉ፡፡




ስእል 8፡ ራባ

የስር ሀላፊነትም ሲኖርባቸው ወታደርም ሆኖ ያገለግላሉ ከሀገር ሮሮ ይከለክላሉ ሲመክቱ የጦር መሣሪያም እራሳቸው ያዘጋጃሉ፡፡

በመደራጀትም ፈረስ ጉግስና ዋና ይለማመዳሉ፡፡ ከዚህ በሀላ ማንኛውም ሀገርን የሚመለከት ጉዳይ ላይ መሳተፍም ይጀምራሉ፡፡

## 2.5 ዶሪ

ዶሪ ወይም ራባ-ዶሪ ከራባ በመቀጠል የሚገባበት እርከን ሲሆን የጎደሉ አባላት ካሉ ተሟልተውና ተጠናክረው ለአንድ ሳምንት ከሚያማክራተው ሽማግሌዎች ጋር አራዳ ጂላ ኡልማ ይገባሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ከሌለው ሰው ጋር መነጋገር ክልክል ነው፡፡ ኡልማ ጨርሰው ሲወጡ ጋደኞችቻቸው እየዘፈኑ የዳኒሳ ቅርጫፍ እየሸለማቸው ሲመና ያረጉላቸዋል፡፡ እነሱም ዳኒሳ ላይ በመቆም አብረው እየዘፈኑ ለጠባቂዎቻቸው ምስገና ያቀርባሉ፡፡

ዶሪን የሚመሩት አዱላ ዶሪዎች ከዚሁ ገሬ ሲመረጡ ተጠያቂነታቸውና ሀላፊነታቸው ፊት አውራሪነትና የጦር አዋጊነት ይሆናል፡፡ ዶሪዎች ጦርነት በሌለበት (በሰላም) ጊዜ ስለሴራ፤ ስለሂራ፤ ስለታሪክ, እንዲሁም ስለባህል በጥልቀት ይማራሉ፡፡

በዚህ ደረጃም ሚስት ማግባትና ቤተሰብን መመስረት የሚጠበቅናቸው ሀላፊነት ነው፡፡ አንድ ሰው የራባ አባል ሆኖ አጥቶ ካጣ አምስት (5) ባለ አራት እግር ከብት ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህንን የሌለው ሰው ጨፋቴ ይባላል፡፡ ጨፋቴ ሀጤ ባይሆንም ለአባ ገዳነት አይታጭም፡፡ ጨፋቴ ለአባ ገዳነት የማይታጭበት ምክንያት ሲጠቅሱም አንድ ሰው ለራሱ የማይሆን ከሆነ ያሰው ለሀገርም አይሆንም ይላሉ፡፡ ስለዚህ ጨፋቴ አባ ገዳ ከሆነ ሀገርንም እንደራሱ ሊያደርግ ስለሚችል ወደፊትም ይህንን ካልሞላ እድሜ ልኩን ራባ እንደሆነ ይቀራል ማለት ነው፡፡ እንዲ ዓይነቱ ሰው ቆሌ /Qolee/ ነው ይባላል፡፤




ስእል 9፡ ራባ

ራባዎች በቀጣይነት ባሊ (ስልጣን) ተቀባይ ስለሆኑ ለመዘጋጀት እንዲጠቅማቸው ራባ ከገቡ ከአራት ዓመት በሀላ ከሰግላን ያኢ (ስልጣን ላይ ያለ መንጋስት) ጋር አብረው የተለያዩ አራዳ ጂላ በመዘዋወር የአስተዳደር የፍትህና ልምድ ይቀስማሉ፡፡ እንዲሁም አንዳንድ ዉስብስብ ያልሆኑ ጉዳዮችንም በሰግላን ያኢ ሞግዚትነት ስር በመሆን እንዲዳኙ ይደረጋል፡፡ ይህም በሚቀጥለው ስልጣን ዘመናቸው ጠንካራ መንግስት እንዲመሰርቱ ይረዳቸዋል፡፡

## 2.6 ገዳ

ገዳ ወይንም ገዶማ ከሁሉ እርከኖች እጅግ በጣም ወሳኝ እርከን ነው፡፡ ይህም የፖለቲካና ማህበራነት መሪነትን የሚጨብጡበት ስልጣን ብቻ ሳይሆን የሀገር እጣፈንታ በእጅ ላይ የሚወድቃበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ እርከን በጣም ወሣኝና እጅግ አስፈላጊ እርከን ሲሆን የገዳ ትልቁ ስልጣን የሚይዝበት እንዲሁም የእምነት መሪነትም የሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡



ስእል 10፡ ገዳ

በዚህ ጊዜ አባገዳ የሚሆኑትና ትልቁን ስልጣን የሚጨብጡት ባለፉት እርከን (ራባና ዶሪ) ላይ ልዩ ችሎታ ያላቸውና የሚደንቁ አባላቶች የተሻለ እድል ይኖራቸዋል፡፡ ይህ እርካን ሀገርን የሚያስደድሩበት እርከን ስለሆነ ሂደቱም በምርጫ ሲሆን ሀላፊነታቸውም ህግን መተርጎም የፍርድ ውሣኔ መስጠት እና ሀገርን ማስተዳደር የሆናል፡፡

## 2.7 ዩባ

ዩባ የሚገቡት ሰዎች የገዳ ስልጣን ላይ ከቆዩ በሃላ ስልጣኑን ለዶሪ አስተላልፈው የሚገቡበት እርከን ነው፡፡ የዩባ ደረጃ ከዩባ I እስከ ዩባIV ደረጃ ሲኖረው ሀላፊነታቸውም እንደዚያው ይለያያል፡፡

ዩባ I እድሜያቸው ከ48 - 56 አመት ድረስ ያሉ ሲሆን ወደ አማካሪነትም የሚመጡበት እድሜ ነው፡፡ ዋና ስራውም የሰግለን ያኢዎች ማማከር ህግን መፍታት የመሳሰሉት ይሆናል፡፡

ዩባ II እድሜያቸው ከ57 - 64 አመት ድረስ ያሉ ሲሆን ተጨማሪ አማካሪ ሲሆን እነሱም ገዳዎችን ያስተምራሉ ይመክራሉ፤ ያስተካክላሉ ያጠነክራሉ፡፤

ዩባ III እድሜያቸው ከ65 - 72 አመት ድረስ ያሉ ሲሆን

የባ IV እድሜያቸው ከ73 - 80 አመት ድረስ ያሉ ሲሆን የሽምግልና ደረጃ ሲሆን ማንጉዶምዎችም ናቸው፡፡



ስእል 11፡ ዩባ

እነዚህ ማንጉዶዎች ከራባ-ዶር ጋር በመሆን አብረው ህግ ማርቀቅ ላይ ይሳተፋሉ እንዲሁም ልጆቻቸው በውድድር ወቅት እንዲያሸንፉም ይረዱዋቸዋል ወይንም ያስተምራሉ፡፡ በተጨማሪም ስለእርቅ ስለስራ ስለእኩልነት ስለፍታዊነትም ያስተምራሉ፡፤ በተጨማሪም ከቃሉ ጋር በመተጋገዝ ባህል፤ ሴራ እና ሰፉ እንዳይታለፍና እንዳይጣስ እየጠበቁ የገዳም ሚሴንሳ አብረው ይመርጣሉ፡፡

## 2.8 ገዳሞጂ

ይህ እርከን ሽማጋሌዎች ጡረታ የሚወጡበት እና ሙሉ በሙሉ ከገዳ ስራ የሚወጡበት ጊዜ ነው፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ የሚደርሱ ማንጉዶዎች በእድሜያቸው ለሶስተኛ ጊዜ ገዳን የሚያዩ ሰዎች ሲሆኑ እንደ እድለኛም ይታያሉ፡፡ ይህም

1. 1ኛው በላጅነታቸው ደበሌ በነበሩ ጊዜ የነሱ ገዳ በስልጣን ላይ እያለ፡
2. 2ኛው እራሳቸው ገዳ የሚሆኑበትና ስልጣን የሚይዙበት ጊዜ ሲሆን፤

3. 3ኛው ገዳ ሞጂ ሆው ልጆቻቸው ገዳ ሲሆኑ ወይም ገዳ ሲገቡ፡፡

ስለዝህም አንድ ሰው በሙሉ እድሜው ሶስት (3) ጊዜ ገዳን ያያል ማለት ነው፡፡ ወደ ገዳሞጂ ሲያልፍ የመሸጋገርያ በአል ሲከበር ይህም የቁንቢ በአል ይባላል፡፡ በዚህ በአል ላይ ትንሽ ትልቅ ሳይባል ሁሉም ይታደማል፡፡ የገዳሞጂ ታሪክም ይዘከራል ለሀገራቸው ያበረከቱት ጀብዶች ይነገራል እንደ ጀግና ይደነቃሉ እነሱም ይሸልላሉ ፡፡ በገዳ ለሀገራቸው ጥሩ ነገር የሰሩ ሰዎች ልዩ ክብር ይሰጣቸዋል ቀሪውን እድሜያቸውንም ተከብረው ይኖራሉ፡፡

*********

መረባ የረቢ ነው¡!

*********

# ትምህርት 3

# የገዳ አስተዳደር ስርአት

## 3.1 መግቢያ

የኩሽ ህዝብ በመካከለኛውና ምስራቅ አፍሪካ የሚኖር ሲሆን በጣም ተቀራራቢ ባህልና እሴትና ያልተላያየ የተገመደ ማንነትም አላቸው፡፡ የኦሮሞ ህዝብም ከነዚ ህዝቦች አንዱየሆነው የኦሮሞ ህዝብም ጠንካራ ማንነት እንዲሁም አብሮ የሚያኖር ባህልና ወግ ባለቤት ነው ይሁንና ለብዙ አመት በተጽኖ ውስጥ እንካን ሆኖ ትስስሩ ሳይበጠስ በሰፉና በዱዳ ይኖራልይህም ሞራላወመና ስነልቦናዊ ግንበሠታ ላይ አሉታዊም ተፅዕኖ አሣድሮለታል፡፡ እሴት ሲያካብት የገዳ ስራአትም የዚሁ ውጤት ነው፡፡ የገዳ ስርአት ዲሞክራሲያዊ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ሲያስረዱ በዚህ ሁኔታም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍልስናውን አያረቀቀ ሄል፡፡

አቶ ዲሪቢ ደምሴ Bulchiinsa ገዳ “Ilaalcha Oromoo” በሚል ፅሁፋቸው በገፅ 200 ላይ የኦሮሞ ይተዳደርበት የነበረው ሄራ እና ሴራ እራሱ ፈጥሮ የተዳደርበት እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ በመቀጠልም የኦሮሞ ሦስት የአስተዳደራዊ ስራአትን እንዳሳለፈ ሲገልጹ እሱም፤

1. የሴቶች ሥሪአት አስተዳደር
2. የገዳ ሥሪአት አስተዳደርና
3. የፌውዳል ሥሪአት አስተዳደር

ገዳ ነፃ በሆነ መልኩ ህዝብን በአንድነት አቀናጅቶና አደራጅቶ የሚያኖር የራሱን መሪ ያለው ተስማምተው ለመኖር እጅግ ጠቃሚ የሆነ እሴት ነው፡፡

## 3.3 ቦኩ ካላቻና ጫጬ

ቦኩ ባለው ዋዳ ህዝብን መምራት በእኩልነት መልኩ አገልግሎት በመስጠት የተጠያቂነት ምልክት ነው፡፡ ቦኩ, የሙሉ የሠው አካል ምልክት ሲሆን ካላቻም ግምባር ላይ ያስራሉ፡፡ እኚህም ህብረተሠቡን ለመምራት ሙሉ በሙሉ የሚታመንባቸው ናቸው፡፡



ስዕል 12: ቦኩ

ማንጉዶ እንደሚሉት, ካላቻ መብረቅ ከወረደበት አፈር ላይ ከሚወጣ ብረት በመጠቀም ነው የሚሠራው፡፡ ይህ ደግሞ ካላቻ ዋቃ በመብረቅ በመጠቀም ስለሚያወረደልን ነው ይላሉ ሀዩዎቹ፡፡ ካላቻ አድረገው የሚሄደው "አባ ካላቻ" ይባላሉ፡፡ ቦኩ የሚይዝ ደግሞ 'አባ ቦኩ ይባላሉ፡፡ጫጬ የባህል መሣሪያዎች ሆኖ ቤራን የሚይዙት ነው፡፡ ጃርሶሊና ቤራን ካላቻ እና ጫጬ በመያዝ እርቅን ያወርዳሉ፡፡በዚህ የመጣ እርቅ አይደፈርስም ጠንካራ የሆናል ይላሉ፡፡ ስለዚህም አባ ካላቻ እና ሀዳ ጫጬ በማህበረሰቡ የተመረጡና ሁሉም የሚቀበላቸው ናቸው፡፡

ካላቻ በእድሜ የገፉ ወንዶችና የጎሣ አንጋፋዎች ግምባር ላይ ሲያደርጉ በህብረተሠቡም ትልቅ ቦታ ሲኖረው ብዙን ጊዜ ካላቻ ያደረገ ሠው በኩ በእጁ ይይዛል፡፡ ካላቻ እርቅ ለማውረድ እንዲሁም ለበአልና ማህበራዊ ጉዳዮችን ለመፈፀም ያገለግላል፡፡

በሌላው መልኩ ዘመድ የሞተበት ሰው መሪር ሀዘን እንዲረሣ ወደ እርቅ እንዲመጡ ያደርጋል፡፡ የእርቅ ምክክር ሲደረግ ሰዎች ካላቻ ና ጫጩ ካዩ ሰላም እንደሚወርድ ያምናሉ፡፡ ይህም የአስታራቂ እርግማን እርቅ ላልተቀበለው የሚደርስ ና ለተቀበሉት ደግሞ ምርቃት የሚደርሰው ትልቅ ስለሆነ ሠዎች እርቁን እንዲቀበሉ ያደርጋል፡፡

### 3.3 አራዳ ጂላ

አራዳ ጂላ የተከበረና ሥፍራ እና ጂላ ገዳ የሚቀመጥበትና የህዝቡን ጉዳይ የሚያዩበት ሥፍራ ነው፡፡ አራዳ ጂላ ብዙ ቢኖርም ኦዳና ጨፌ ይዘወተራል፡፡ ኦዳ የሠላም ምንጭና የአንድነት ምልክት ነው፡፡ ኦዳ ማለት እርጥብና ትልቅ ከራሱ ተርፎ ለሌሎች የሚሆን ሲሆን ከእንጨቶችም የተከበረና የተመረቀ ነው፡፡ የኦዳ ተክል በጣም ለምለም ሲሆን እድሜውም በጣም ረጂም ነው፡፡ ይህ ተክል ምንም ያህል ድርቅ ቢበረታ አይደርቅም በመሬት ስር በመሄድ ውሃና እርጥበት ያለበት ቦታ ላይ ይበቅላል፡፡ አስተዳደጉም የተወሰነ ከፍ ካለ በኃላ ወደጎን ስለሚንሰራፋ ለሠዎችና ለከብቶች ጥላ ሆኖ እንዲያገለግል ይረዳዋል፡፡



ስእል 13፡ ኦዳ

ማንጉዶዎች ኦዳ እንዴት እንደተመረጠ እንዚህ ይገልጿሉ፡፡ ድሮ ድሮ ድርቅ ሲጠነከርንባቸው አንድ ሽማግሌ ከብት እያበላ አንደኛው ጎሮምሳ ይጠፋበታል፡፡ ሰውየው የ ጎሮምሳውነን ፋን በመከተል ፍለጋ ይጀምራል ፡፡ ሲፈልግም ኦዳ ስር ተኝቶ አገኘ

ይህም ሽማግሌ ጎሮምሳ በማግኘቱ ተደሰተ የኦዳው ጥላ ስር አረፍ አለ፡፡ ወዲያው ደመናው ኦዳውን ከበበው፡፡ ዋቃዮ ሴራና ሰፉ ሰዎች ማክበር ያለባቸውን እዲሁም ከ ጩቡ እራሳቸውን የሚጠብቁበት አወረደላቸው፡፡ ከዛ ጊዜ ጀምሮ ይህ ሽማግሌም የዋቃን ኢማና የተሰጠው ለመወጣት ኦዳ ስር ሆኖ ማስተማር ጀመረ ፡፡ ኦዳ ገልማ አባ ገዳ ሲሆን በተለያዩ አካባቢዎች ስለሚገኝ አረዳ ጂላ ሆኖም ያገለግላል፡፡ ኦዳ የአያና ሙዳ እና አያና ጩኡምሳ የሚፈፀምባቸውና የገዳ ሚሴንሳ የሚደራጁበት ቦታና የአቦቲ ገዳ መቀመጫ ነው፡፡

ሁሉም ኦዳ በአንድ አመት አልተደራጀም እንዲያውም አንደኛ ከሌላው እየተገነጠሉ ቅርንጫፍ ንዑስ እየሆኑ እራሳቸውን እየቻሉ ሄደዋል፡፡ ታላቁ ኦዳ ኦዳ ሮባ ሲሆን ኦዳ ነቤ የኦዳ ሮባ ቅርንንጫፍ ነው፡፡ እስከ 1558-59 የመጫና ቱለማ በአንድ ላይ ኦዳ ነቤ ስር ሴራ ደንግገው ያውጁ ነበር፡፡ በኃላ መጫ እራሱን በመቻላቸው ኦዳ ቢሲል በማደራጀት ለጂላ ኦዳ ነቢሲልን መጠቀም ጀመሩ፡፡ የአርጋ ዳጌቲ ታሪክ እንሚነግረን, ኦዳ ቢሲል የግጊቤን ወንዝ ቢሎና ጌዶ መሀል እንደ ተደራጀ ይነገራል፡፡ አካባቢ ውም በተራራ ተከቦ ሲገኝ፡፡ የቢሲል ኦሶሌ የሚባል ሰው ይዞታ ላይ ስለ ነበርና ስሙንም ኦዳ ቢሲል በሱ ስም እንደ ተሰየመ (ታንሳንያሜ) ይነገራል፡፡ የኦዳ ቢሲል መሪና አስተዳደር የነበረው መኮ ቢሊ ብዙ ሴራ ያፀደቀ ሠው እንደሆም ሲነገር አምስቱ መጫዎችም እዛ ስር ይገናኝም እንደነበርም ይነገራልር፡፡ ለብዙ አመታት የገዳ ማእከል በመሆን በማገልገል ብዙ ሴራ የተደነገገበትና ያኢ የሚደረግበት የነበረው አምስት ሲሆኑ እነሱም፡

1. ኦዳ ሮባ: - ባሌ ውስጥ ይገኛል፡፡
2. ኦዳ ነቤ:- ሸዋ ውስጥ ይገኛል፡፡
3. ኦዳ ቢሲል: - ሸዋ ውስጥ ይገኛል፡፡
4. ኦዳ ቡልቱም: - ሀረርጌ ውስጥ ይገኛል፡፡

5. ኦዳ ቡሉቅ: - ወለጋ ውስጥ ይገኛል፡፡

### 3.4 አዱላ ገዳ

አዱላ ገዳ የገዳ አስተዳደር ውቅር ሲሆን ከ 6-9 የአባላት ብዛት ኖሮት በሦስት ስራ አስፈፃሚ ይመሠረታል

1. የሀገር ጨፌ (National Legislation)
2. የጎሣ ጨፌ (Provincial Legislation)
3. የአከባቢው አስተዳደር ጨፌ (Local Legislation)

### 3.5 ሰግለን ያኢ

ሰግለን ያኢ ማለት ገዳን የሚያስተዳድሩ ሰዎችን ማለት ሲሆን ቁጥራቸውም ዘጠኝ ነው ፡፡ በየ ስምንት አመትም የገዳን ስልጣን ይረካከባሉ፡፡ ሰግለን ያዒ አባለት እንደሚከተለው ይዳሠሳሉ፡



ስእል 14፡ ሳግላን ያኢ ጋዳ

**አባ ቦኩ:**

አባ ቦኩ /አባ ኮርማ/ Presdent/ የአባአስተዳደር መሪ ሲሆን ሳግላን ያዚን ይመራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፤

- በህዝብ መሀል የሚፈጠር ግጭት ያረጋጋል፤ ያስታርቃል፡፡
- ሀገርን የሚያጠፉ ጠላቶች ሲመጣ አባ ዱላ ይሰይማል ጦርነቱንም ያዛል፤

- የፓለቲካ ውይይት በጨፌ (ጉሚ) ሲደረግ በምርቃት ይከፍታሉ
- የባሊ መቀባበል ስነስርአቱን ይመራሉ፡፡



ስእል 15፡ አባ ቦኩ

አባ ገዳ ባሊ ሳይሠጥ ከሞተ የገዳ ሥርአቱ የሚተከካበት መንገድ አለው፡፡ የዘመናዊ አስተዳደር ሴራ ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስር ሲያልፉ ፖርቲው አስቸኳይ ስብሠባ ጠርቶ ይወስናል፡፡ይህ ሁኔታ ሀገራችን በ2004 የገጠማት ትውስት ነው ፊንፊኔ, ነሀሴ 3 /2010 ፋ.ብ.ኮ፡፡

በሌላ መልኩም አባ ገዳ ሊሆን ያለ እጩ ከሞተ ሀዩ ተማክረው ጠንካራና ህዝቡ የሚያምኑ ሠው ይቀባ ይወሠናል፡፡ ይህን ሁኔታ ለመታደግ አምስት ጎጌሳ ገዳ ይመረጣና ራባ ከሆነ ጊዜ ጀምሮ ስድስት ሀዩ አዱላ ከተመረጡት ውስጥ ወደ ገዳ ያልፋል፡፡ ውስጥ የአባ ገዳ ምክትል ናቸው ይባላል፡፡

- ወንድም ሊሆን ይችላል
- ከጎሳ ውስጥ ይፈለጋል
- ከአዱላ ውስጥ ይፈለጋል

- ሚልኪና ሰፉ ያለው ሰው ይፈለጋል
- አጠቃላይ የኦዳ ምርጫ ይደረጋል

ሰባት ሠዎች ተመርጠው ለ27 ቀን አጋላ ይገባለሉ፡፡ ስልጠና መግባት ማለት ነው፡፡ ይህም አጥር ተሠርቶ በውስጡ ቤትም ተሠርቶ ልክ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንደሚባለው ክተት ስልጠነና ይገባለ፡፡ ሁሉም የራሱ የሥራ ድርሻ አለው ከሠባቱ ውስጥ አንድ ጠንካራ ለፍትሕ አስፈፃሚ ይመረጣል በ'ነላ ወደ መሪነት ይመጣ፡ ሁለተኛው ጃልኬያን የፍትህ ምክትል ሲሆን የፍትሕ ተወካይ በመሆን ያገለግላል፡፡ የተቀሩት በተራ ፋጋ፤ ሀዩ፤ ቃሙራ፤ ቶርቢ እና ጃልdhaባ ይባላሉ፡፡



ስእል 16፡ አባ ቦኩ Iኛ

### አባ ቦኩ Iኛ

አባኮርማ 1 እንዲሁም ኮርማ 1 ይባላል፡፡ ይህም የአባገዳ ምክትል አስተዳደር ነው፡፡ ስራው በሙሉነት አባ ዳውንማገዝ ይሆናል፡፡ ገዳ ባሊ ሲወስድና ሲሰጥ ብዛት ያላቸው ሠዎች አላዳ ያድራሉ፡፡ እነዚህ ሰግለን ያኢዎች የገዳ አስተዳደራዊ ስራን ለመስራት ስምንት አመት ሙሉ ብዙ አራዳ ጂላ ውስጥ ይዘዋወራሉ፡፡ አባ ገዳ ባሊ በሚያስተላልፉበት ዝግጅት ላይ

ብዛት ያላቸው ሰዎች አራዳጂላ ያርፋሉ ይህም ሁኔታ ያኢ አዳ ቡሌ ይባላል፡፡

3. አባቦኩ 2ኛ

ሁለተኛው ምክትል  አስተዳደር ነው፡፡

4. አባ ሙዳ

አያንቱማ  ያለው ቃሉ ሲሆን ጠላት ሀገር ሲያጠፉ ረቢን የሚለምኑ እንዲሁም ለጦርነት ሲወጡ የሚመርቅ፡፡

5. አባ ዱላ

የጦር ሚኒስትር የሠራዊቱ መሪ ፡ የውጊያ ስልት የተካነ በአባ ሙዳ የሚቀባ ፈረስ መጋለብ ሠፊ ብቃት ያለው ፡፡

6. አባ ሎኒ

ቤኛ የሚጠብቅ የገዳን ሰዶ እና ወታደሮች የሚቆጣጠር፡፡

7. አባ ሴራ

የገዳውን ሴራ የሚደነግግና የሚያተረጉም እንዲሁም ሴራውን ስራ ላይ መዋሉን መቆጣጠር፡፡ ከሚመለከታቸው አካለት ጋር ከአባገዳ እና አዱላ ገዳ ጋር ፍትን ፍትህን መስጠት፡፡

8. አባ አለንጋ

የጨፌ ቱማውን (ድንጋጌን) ወደ ሥራ የሚያስፈታ እና  አለጋ በእጃቸው የሚይዝ፡፡ እነኚህ ህግ እንዳይጣመም የሚጠብቁ እንዲሁም በሀቃ ህግ ስራ ላይ እንዲውል የሚያደርገው የህግ መጓደልና የሚያስጠብቁ ናቸው፡፡ በህግ ላይ የሚታየውን ክፍተት ይከራከራሉ የሀዮታ ገዳ ውሳኔም ለጨፌው ያቀርባሉ፡፡

9. አባ ጨፌ

አባ ጨፌ የጨፌ ቃና ሀላፊ ሲሆን ስራውም ጨፌ ላይ መቆጣጠር ተጠያቂነት መውሰድ ነው፡፡ አባ ጨፌ ለጨፌ ሲሆን

ለድሩሬም አባ ድሬ, ለመልካም ደግሞ አባ መልካ ተጠያቂነት ይወስዳል፡፡

## 3.6 የባሊ ርክክብ

ገዳ የገዳ ሰዎች እጅ ላይ ይኖራል የገዳ መደምሰስ ካጋጠመው በኃላ አንዳንድ አካባቢ ሲቀር የተቀሩት አካባቢዎች ላይ ደግሞ በወራና በጎሣ እንዲወረስ ሆኗል፡፡ ይህም በሁሉም ህዝብ ዘንድ እንዳይወሠድና እንዳይተገበር ቢሆንም ስርአቱን ግን አልለቀቀም፡፡ ይህም ከስምንት አመት በኃላ ገዳ ወደ ዶሪ ያስተላልፋል፡፡



ስእል 17፡ ማጋላታ እየነፉ የሚቀርቡ ያኢ

ይህ ሲሆን ባሊ የሚወስድ ቀዬ አባ ገዳ ሲደርስ መጋላታ ይነፋሉ ተዘጋጅቷል ወይ ይላሉ፡፡ ባሊ የሚሠጠው ደግሞ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት መጋላታ ማስጠንቀቂያ ይነፋሉ፡፡ ይህ መጋላታ አራት ጊዜ ሲነፋ ሁለቱም እርስ በእርስ ይመላለሣለሉ፡፡

- የመጀመሪያ ማጋላቲ ተነሱ ለማለት ሲሆን፡፡
- የሚቀጥለው ከብቶችን አሰማሩ ለማለት ነው፡፡
- ሦስተኛው ቀርበናል ለማለት ነው፡፡
- አራተኛው ደርሠናል ለማለት ነው የሚነፋው ፡፡





ስዕል 18: አባ ገዳ ባሊሲሰጥ

ባሊ የሚሰጡ ምራብ ያርፋሉ, ባሊ የሚወስደው ደግሞ ምስራቅ ይሠፍራሉ፡፡ ባሊ ለመውሰድ የሚመጡ ከፈረስ አገሎ ቢልቢላ ባለው ይመጣሉ፡፡ ባሊ ወስደው መመለስ የተነሳው ለአባ ገዳ ሣይሠጡ ቁጭ ብሎ እንዲ በማለት ይማጸናል "ዋቃ ገዳ አውጣ"፡፡

ባሊ ለመውሰድ ከፈረስ ላይ ወርደው "ገዳ! .....! ገዳ ሀገር!" እያሉ ባሊ ወስደው ከፈረስ ላይ ከራሱ ያኢ ጋር ይሂዳል፡፡ ባሊ የሚወስድ ቀን የደስታ ቀን ሲሆን ለሶስት ቀን ስርአቱ "ኡልማ" ይቀመጣሉ ወደ ውጭም አይወጣም፡፡ አቦቲ ገዳ ባሊ የወሠዱ

ስራ ለመጀመር አዋጅ ያሰነጋራል፡፡ አባ ገዳ ባሊ ከሠጠ በኃላ አባ ሴራ ስለሚሆን ዩቦሜ ይባላል፡፡ ቀጣይ ራባ ዶሪ ጋሜ ....ሆኖ ከስር እያደገ ይሄዳል ወደ ላይ እየመጣ መጥተው ለሀላፊነት እራሣቸውን እያዘጋጁ ሀዩና ማካላ አባ ገዳ በስራ የሚያግዝ ይመርጣሉ፡፡ ባሊም ከኦላ በአንድ ላይ ነው የሚቀበሉት እንዲሁም በአንድ ለመስጠት፡፡

ስለ ባሊ ከአርጋ-Dha-ጌቲ እንደሰማነው፡ የገዳ አያንቱ ለሁሉም ሁሉንም ነገር አካፍለዋል ቦናያ ምርቃት ካለቀ በኃላ የአረደውን ስጋ ለሁሉም ካከፋፈለ በኃላ, ቦነያ እኔ ምንም አላገኘም?" ሲል "ይህንን ባሊ ሰተንሀል" አለ ይባላል፡፡ ከዛ በኃላ ፀሀይ በሁሉም ጠነከረ ጥላ ፈልገው ሲሄዱ ቦነያም ሂዱልኝ አላቸው፡፡ ዝናብም ሲዘንብባቸው እንዲሁ ለመጠለል ሲመጡ ሂዱልኝ አላቸው አሁንም፡፡ ከዛ ሁሉም ነገር ተመርቆ ቢሠጠንም ጥላ ግን በሌለበት ቦተሠ ዋጋ የለውም ብለው ተማከሩ ከዛ ቦነያም ጥላ እንሠጣቸው እነሡም እሡ ያጠሠውን ሁሉ አካፍለውት ሁሉን ነገር አሸንዲጠቀም ፈቀዱለትና አብረዋቸው መኖር ጀመሩ፡፡ ባሊ ሲቀባበሉ ሁሉም የተመረቁበትን ነገር ይዘው ሲመጡ ቦነያ ግን ባሊ ይዞ ይወጣል፡፡ በባላ አሸነፈ ብሎ ያቅራራባቸዋል፡፡

ባሊበወረሃ ጉራንdha-ላ ውስጥ የሚቀባበሉ ሲሆን መቀባበያ ጊዜ ሲቃረብና ደርስ ባሊ የሚሰጡና የሚቀበሉ ተራርቀው አራዳ ጂላ ያርፋሉ፡፡ አባ ገዳ ሚስቱና ሚንጂዎቹ ጋር አብረው በመሆን ባሊ አብረው የሰጣሉ፡፡

የሽማግሌ ምርቃት ባሊ ሲሰጡ

የሚሰጠው "እንካ ባሊ" ይላል

የሚቀበለው ደግሞ "ስጠኝ ባሊ" ይላል

እንካ ባሊ!

ስጠኝ ባሊ

የገዳ አባቶች ባሊ ሲቀባበሉ የመራረቃሉ:

አብረን  እንኑር

ተከባብረን እንኑር

እርባታን እለፈኝ

ኑሮን እለፈኝ¡!"


አብረን እንኑር

ጥጋብን እለፈኝ¡!"

እያለ የቀድሞ አባ ገዳ አዲሱን አባ ገዳ ይየመርቃል፡፡ ገዳ ባሊ እንደ በልጠውም ይመርቀዋል፡፡ አንድ ገዳ ስምንት አመት የሚቀባበሉ ሲሆን የራሱ የሆነ ስምም ይኖረዋል፡፡

### 3.7 ጎጌሳ ገዳ

ገዳ አምስት ጎጌሳ ሲኖረው አምስቱ ገዳ ይባላል እነኚ ገሬዎች በየስምንት አመታት ስልጣን ይይዛሉ ገዳን ይቀባበላሉ የየራሳቸው ስምም ይኖራቸዋል፡፡ የትኛውም ሠው ከተወለደበት እስከሚሞት ጊዜ ገዳ ውስጥ ይኖራ፡፡ ከአምስቱ ጎጌሳ ገዳ ውስጥ የአንደኛው አባል ሆኖ ይታቀፋል፡፡ ይህም እሱ ሲወለድ በስልጣን ላይ ያለው ገዳ አባል ሆኖ ሲታቀፍ የአባቱን ጎጌሳ ውስጥ ይሆናል ማለት ነው፡፡




ስዕል 19: አዱላ ገዳ

*********

መረባ የረቢ ነው።!

*********


# ትምህርት 4

# የፊና ሥርአት

## 4.0 መግቢያ

የኦሮሞ ህዝብ በመካከለኛውና ምስራቅ አፍሪካ ለብዙ ሺ አመታት ሲኖር የነበረና እየኖረ የሚገኝ ባለ ትልቅ እሴትና ባለሙሉ ፀጋ ህዝብ ነው፡፡ ይህ ህዝብ ኢኮኖሚውን የሚያፈራበትና የሚጠብቅበት ሥርአት ብዙዎቹ ዛሬ ላይ የሚታወቅ ባይሆንም ብዙ እንደነበሩ በአርጋ ዳጌቲ ሲተላለፍ መቷል፡፡ የኢኮኖሚና የማዕከላዊ እሴት በጣም ሰፊና ጥልቅ ነው ይህም ከብዙ አመት ልማድ ድርጊት እና ክስተት የሚወለደው እድሜ ጠገብ እውቀት ነው በትውልድ እየተሸጋገሩ ልምዶችን በመጨመር አዳዲስ ክስተቶችን በማጤንና ከግንዛቤ በማጠናከር ሠፊ እውቀት መፍጠር የቻለበትን እውቀት ለኢኮኖሚው ማደራጃ ፍልፍና ተጠቅመውበታል፡፡ ይህ በመሬት ላይ የወረደና የተፈተኑ እውነታዎች የፊና ገዳ ሥርአት ይባላል፡፡ይህ ፊና የማህበራዊ የፀጋንና ሀብትን እሴትን መንከባከብና መጠበቅ ሥርአት ሲሆን ፊና-ፊናቹ የትውልድና የእያንዳንዱ ዜጋ ሀላፊነትና ግዴታ ነው፡፡ የፊና ገዳ ሥርአት ሰባት ደረጃዎች ሲኖሩት እድገቱም ከአንድ በመውጣት ወደሚቀጥለው ደረጃ ይሸጋገራል፡፡

የአንድ ዙር ወይንም ደረጃ ጊዜ በተወሰነ ጊዜ ባይከለልም ከተወሰነ ጊዜ ቆይቶ ወደሚቀጥለው እርከን ይሸጋገራል፡፡ ይህ ሲሆን ጥንካሬውም የዛኑ ያህል እየጠነከረና እየከበሩ እየከበዱ ይሄዳል፡፡ ይህም በራሣቸው እንዲቆሙ ይረዳሉ፡፡



ስዕል 20: የፊና ደረጃዎች

### 4.1 ፈጫሳ

ፈጫሳ የመጀመሪያው የፊና ደረጃ ሲሆን የቆይታ ጊዜው እንደ ሁኔታው ይወሰናል፡፡ ይህም ልክ አንድ ዘር እንደሚዘራው አይነት ይታያል፡፡ ይህም ዘር ከመዘራቱ በፊት መሬቱ መለስለስ ውሃ አቅርቦት ቦይ ማውጣት ብቻ ሁሉም አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ ማድረጉ የዚን ደረጃ በተገቢ መልኩ እንዲሠራ ይረዳል፡፡ ስለዚህም ዘር ከመተከሉ በፊት ምንላይ መተከል እንዳለበት መቼና የት መተከል እንዳለበት ማወቅና ወስኖ እንደሚተከል ማድረግ ዘሩ ለቡቃነት ጥሩ ግብአት እንዲሆን ይረዳዋል፡፡ ይህ ደረጃ ልጆች ለእናት ለአባት በመላክ ስራን የሚለምዱበት ደረጃ ነው:: ልጆች በፈጫሳ ደረጃ ልጆች የሰፉ መሠረታዊ አሴቶችን እንዲሁም ታሪክ አባባል ተረት ይማራሉ፡

### 4.2 ቢቂላ

ቢቂላ ሁለተኛው ፊና ሲሆን መልካም የፋጫሳ ደረጃ ያለፈ በጥሩ ሁኔታ ወደ ቢቂሉ ያልፋል፡፡እዚህ ላይ ልጆች ክፉና ደግን ጥሩና

መጥፎን ዘመዶቻቸውን እና የዝምድና ሁኔታን ማወቅ ዘፈኖች ሽለላ ቀረርቶና dhaዳኖ ፈረስ መጋለብ እስፓርታዊ ውድድሮችን ይለምዳሉ፡፡ ስለመብትና ግዴታ ይማራሉ ስለ ፖለቲካና አስተዳደር ይማራሉ፡፡

## 4.3 ጉዲና

ጉዲና ሦስተኛው የፊና ደረጃ ሲሆን ጥንካሬን ያሳያል አካላዊና መንፈሳዊ ጥንካሬ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ይህንን ደረጃ የሚደርሱ ሠዎች የሁለቱን ደረጃ በሚገቡ አልፈው የመጡት ናቸው፡፡ በዚህም ጊዜ የበጎፈቃደኝነት ቅን አሣስበዋል ቢነት ትልቅ ቦታ ይይዛል፡፡ እንዲሁም የሚሠሩት ሥራ ረቢ የሚወደውና ቀጣይነት ያለው መሆኑን ማጤን ተገቢ ነው፡፡ በህዝብ መወደድ መመረጥ እንዲሁም ህዝብን መጥቀም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ የራስን ጥንካሬና ጀግንት እንዲሁም እዉቀት ማሳየት፡፡ ጉዛ ዳቦ እንዲሁም ማሂቤራዊነት አገልግሎት መስጠትና ህግን አለመጣስ፡፡ በህዝብ ላይ የሚደርስ ሮሮ መከላከልና ማስከበር፡፡ የህዝብን ፍላጎት ማሳካት፡፡ የህዝብን ጥቅም ማስቀደም፡፡ መረዳት የሚገባውን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መርዳት፡፡ ለምሳሌ የተራነበን ማብላት የተጠማን ማጠጣት ዳራ ባሱ ልጆችን፤ ሴቶችን፤ ማንጉዶን፤ ጃማን ውሃ /ወንዝ/ ማሻገር፡፡

## 4.4 ፉርዲና

ፉርዲና ደረጃ አራተኛው የፊና ደረጃ ሲሆን ከወጣትነት ወደ ወሳኘኝና ሀላፊነት የሚሚመጣበት ደረጃ ነው፡፡ እዚ ጋር የማይነቃነቅ ዋልታ የሚተከልበትና ለወገን መከታ የሚኮንበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ያሉ ሠዎች እራሳቸው ብቻ ሣይሆኑ ልጆቻቸውም ጭምር ታማኞችና ቅን ሠዎች ናቸው ፡፡ ዋስ የሚኮንበት ደረጃ ነው ይህ እርከን ፡፡ ይህም አንድ ሠው በማህበሩ ውስ ጥፋት ሲያጠፉና ዋስ ጥራ ሲባል የሚጠሩ አይነቱ ሠው ነቸው እዚህ ደረጃ ላይ ያሉት እነኚ በአጥፊውና በተበዳዩ መሀል ለመግባት የሚችሉና የሚታመንበት ሠው

ናቸው፡፡ አጥፊውም ሆነ ተተበዳይ ይሠሟቸዋል፡፡ አስታራቂዎች የሠፈሩ አስተዳደር የጎሣ መሪ፡፡

## 4.5 ጋቢና

አምተኛው የፊና እርከን ሲሆን የራሱ የሆነ የጊዜ ቆይታ ይኖረዋል፡፡ የህም የመስፋፋት እና የማበቢያ ጊዜ እንደማለት ይሆናል፡፡

## 4.6 ባዳዲና

ስድስተኛው የፊና እርከን ሲሆን የራሱ የሆነ የጊዜ ቆይታ ይኖረዋል፡፡ የህም የመድረስና እና የማፍራት ጊዜ እንደማለት ይሆናል፡፡

## 4.6 ዳጋጊና

ይህ ደረጃ ሰባተኛውና የስኬት ቁንጮ ላይ የሚቀመጠው ደረጃ ሲሆን ብዙውን ጊዜ በጎሣ እንጂ አንድ ሠው ብቻው የሚደርስ በት ደረጃ  አይደለም ዋራዎች የሚያገኙት ዝና ስም ክብር ነው፡፡ አያቶቻቸው እንዲሁም አባቶቻችን ትልቅ ደረጃዎች ያሉዋቸው ሠዎች ናቸው፡፡ ይህም በስማቸው ሀገር ሆራ ይሠየምላቸዋል፡፡ የሰራሳቸውን ብቻ ሣይሆን ቤተሠበቡ የሞተው የአቅም ደካማ ሠዎችን ልጅ የሚያሳደግ መንገዶች የሚያረሳድር፡፡ የባሊመቀበልና መሥጠት ሥርአት ላይ ቃሉ በዘራቸው ያለ ብዙ አያንቱ ልጆች ያሏቸው፡፡

*********


መረባ የረቢ ነው!!

*********

# ትምህርት 5

## አያና

አያና በዋቃና በሰው መሀከል ያለና ዋቃም ሠውን የሚያይበት ተፈጥሮአዊ የሆነና ማንም ከሠው ላይ መግፈፍ የማይችል ሲሆን ሶስት አይነት ነው፡፡ ይህም አያና ኡማ አያና ኡማማና አያና ኡማታ ናቸው፡



ስእል 21፡ አያና

አያና ሌሎች ትርጉሞች ያለው ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ጮራ፤ ሚልኪ ክብረ በአልም እንደማለት ይሆናል፡፡ ሁሉም ፍጥረት የራሱ አያና ያለው ሲሆን በአይን ማየትም አይቻልም (አይታይም)፡፡ በህይወት ያለፈ (የሞተ) ሠውና ሀራሙና ጨጸና የሠራ ሰው አያና ይርቀዋል፡፡ አያና በአያና ብቻ የሚታወቅ ሲሆን ሰዎች ሰፉን በመፈጸም አያና ይጠብቃሉ፡፡ ሰፉ ማክበር ደግሞ ሁለንም ነገር የሚያስተካክል የዋቄፈና መሰረት ነው፡፡ በሌላ መልኩ አያንቱ የሚባሉ ሰዎች ደግሞ ቃሉ ሳይሆኑ በዋቃ ልዩ ስጦታ የተቸራቸው ናቸው፡፡ እነዚህም የነኩትና የሰሩት ነገር ሁሉ የሚባረክላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ብዙ አያንቱዎች ሲኖሩ ከነዚህም እንደ ማሊማ፤ ዋታ፤ ኤኬር-ዱቢፍቱ፤ ሞራ-ላልቱ እና ሌሎችም ይኖራሉ፡፡

ማሊማ የራሱ ታሪክ ያለው  አያንቱ ውስጥ አንዱ ሆኖ በኩርነትን በደግነቱ ከዋቃ ያገኘ ነው፡፡ እነኚ ብዙውን ጊዜ ምላሳቸው ጥቁር የሆኑ ሰዎች ሲሆኑ ከመረቁም ሆነ ከረገሙም የሚደርስ ነው፡፡ ማሊማዎች ድርቅ በበዛበት ጊዜም ዝናብን የሚለምኑ እና የሚያዘንቡ እንዲሁም ዝናቡ ያለጊዜ ካልቆመ እንዲያቆም የሚለምኑና ዋቃ የሚሰማቸውና ለማቆምም ልዩ ብቃት የሰጣቸው ሲሆኑ አንዳንድ ቦታ ጫምሲቱ ይባላሉ፡፡

ሌላ የአያንቱነት ተሰጦ ያላቸው በህይወት ያለፉትን (የሞቱትን) ሰዎች በአያና የሚያናግሩ አያንቱዎች ሲሆኑ ለቤተሰብና ለጎረቤት መልዕክትና ምክር የሚለግሱ ናቸው፡፡ ይህም አንድ ሰው በህይወት አልፎ “Miju Dhibayuu” ሳይወጣ የኤኬር-ዱቢፊቱ ቄኤ በመሄድ የኤከራን መልዕክት ይሠማሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የሞተውን ሰው ኤከራ ለሞቱ ምክንያት ምን አይነት ነገር እንዳገኘውና ለወደፊትም ያ ቤተሰብ ከምን እራሱን መጠበቅ እንዳለበት መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ እነኚህ አያንቱዎች ሌሎች ሰዎች ማየት የማይችሉትን ነገር ባላቻው አያና አማካይነት የሚያዩና ልዩ ችሎታ ያላቸው ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ እጃቸውና ትንፋሻቸው መድሀኒት የሚሆንና ሰውነትን  የሚያሹ (ኦጌሳ) እንዲሁም ለታመመ መዲሀኒት የሚሠጡና ለተለያዩ ችግሮች የሚመክሩም አያንቱዎች አሉ፡፡



ስእል 22፡ የመድሀኒት ድንጋዮች

## 5.2 የDHA-ሀ ገዳ ሥርአት

የኦሮሞ Dha-ሀ የየኦሮሞ ህዝብ እንዴት ቀን ወርና አመታት ን የሚቆጥሩት ስሪአት ነው፡፡ ይህ Dha-ሀ ከክርስቶስ ልደት 300 አ. አ በፊት የተፈጠረ ሲሆን በወር ውስጥ 29.5 ቀን ሲኖር በአመት ውስጥ ደግሞ 12 ወርና 354 ቀን ይኖራል፡፡ ይህ Dha-ሀ ሳምንት የሌለው ሲሆን በወር ውስጥ ያሉት ቀናት እያንዳንዳቸው ስም አላቸው፡፡

የቦረና Dha-ሀ በጨረቃ በኮከብ እና በጸሃይ ይወሰናል፡፡ ከኩሽ ህዝቦች ውስጥ አንዱ የሆኑት ኦሮሞ ራሱን dha-ሀን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ300 ዓ.ዓ አካባቢ እንደፈጠሩ ይታመናል፡፡ በሰሜን ኬኒያ የሚገኙ ናማራቱንጋ 1 የአሪኪዮ-አስትሮኖሚ ጥናት ውጤቶች ምስክርነት ይሠጣሉ፡፡ እንዲሁም ናማራቱንጋ 2 በቱርካና ሀይቅ አካባቢ የሚገኙ 19 የቁም ድንጋዮች ወደ 7 ከዋክብት አቅጣጫ የሚያመለክት dha-ሀን ያሣያሉ፡፡ ይህ ከባዛልት የተሰራ የቁም ድንጋዮች በ7 ከዋክብቶች አቅጣጫ ሆኖ ይታያል፡፡ እነዚህ ከዋክብትም ኡርጂ ለሚ (Triangulum)፣ ኡርጂ ቡሣን (Pleidades)፣ ኡርጂ አልጋጅማ (Bellatrix)፣ ኡርጂ ባካልቻ (Aldibaran)፣ ኡርጂ አርባ ጋዱ (Central Orion)፣ ኡርጂ ዋላ (Saiph)፣ እና ኡርጂ ባሳ (Sirius) ይባላሉ፡፡



ስዕል 23: ናማራቱንጋ የባዛልት ጥርብ ድንጋይ

የኦሮሞ dha-ሀ የሚያዩት ናማራቱንጋ በሚገኙ ድንጋይ በመጠቀም ነው፡፡ የdha-ሀ ጥበብ እጅግ ውስብስብና ለሂወት በጣም አስፈላጊ እሴት ሲሆን የdha-ሀ ኮከብ የሚያይ የdha-ሀ አያንቱ ነው፡፡ የህም የሚያይበት የተለየ ተሰጦ አለው፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ከሁለት ሺ አመት በፊትም ጭልጥ ያለ የአስትሮኖሚ እውቀት እንደነበረውና ይህም ለአለም የጊዜ፣ የወራትና የአመት ቀመር ያበረከተ ህዝብ መሆኑን የNASA ሳይንቲስቶች አረጋግጠዋል፡፡

በተጨማሪም የአሜሪካን የጠፈር ምርምር ቡድን በኢትዮጵያ ቦረና በኬኒያ ቱርካና ሀይቅ አካባቢ እንዲሁም በሱዳን ሜሮኤ አካባቢ በተደረገው የአርኪዮሎጂ ጥናት ተመሳሳይ የሆነ ቅርስ ተገኝተዋል፡፡ የኦሮሞ dha-ሀ የኮከብ የጨረቃና የፀሃይ አቀማመጥን በመመልከት፡፡

- ቀናትን
- ወራትን
- አመታትን
- የትውልድ ጊዜን
- የገዳ አመትን ወርን ቀኑንም ጭምር
- ጎጌሳ ገዳ ለመቁጠር
- የአያና ቀንን ለመወቅ
- የአያና ወርን ለማወቅ
- ባሊ የሚሰጥ ወርን ለማወቅ
- ባሊ የሚሰጥ ቀን ለማወቅ
- ገዳን ቆጥሮ ለማወቅና ለመለየት የሚውል ነው ዳሀ፡፡

ይህም ኩሾችን የቱባ ባህል አውቀትና እሴት ባለቤት ያደርጋቸዋል፡፡አለም በጨለማው ዘመን ውስጥ ሲኖርና በድንጋይ ዘመን እንኳ ቋጥኞችን እየፋላንፋለ ቅርጻ ቅርጾችንና ሀውልት የሚሰሩ ሲሆን ገሚሶቹ አሁንም የቱሪስት መደረሻ

በመሆን የያኔውን የኩሽ ህዝብ አለማችን የእድገትና ስልጣኔ ማማ የሆነበትን ያሳያል፡፡




ስዕል 24: የቱሪስት መዳረሻ ቅርስ


እንደዚ Dha-ሀ በጨረቃ መውጣት ወር ሲቆጥሩ በአንድ ወር ውስጥ 29.5 ቀናትና በአመት ደግሞ 12 ወራት ይኖራሉ፡፡ ይህም፡

- የጨረቃ መግባት
- የጨረቃ ትልቀት
- የጨረቃ አቀማመጥ
- የቡሳ ኮከብ እይታ በመመርኮዝና በማጥናት
- ባካልቻን በማጥናት
- በደንብ በመከላከል
- እንዲሁም የፀሃይ ቦታና የጨረራ ሀይል በማጥናት ይሆናል፡፡

ይህ Dha-ሀ የኮከብ የጨረቃና የፀሃይ dha-ሀ ላይ በመመርኮዝ ሲሆን በሰባት ከዋክብት ይወሰናል፡፡

### 5.2.1 ኡርጂ ለሚ (Triangulum)

ኡርጂ ለሚ ከሦስት ተመሳሳይ ኡርጂ የሚዋቀር ሲሆን በጣም አንፀባራቂ ኡርጂዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ከዋክብት ቀጠን ብሎ ረዘም ያለ ነው፡፡ ይህም በአቀማመጡ ሶስት ማእዘን በመስራት ሲሆን በወርሀ ቢቶቴሣ ይታያል፡፡ ይህም የአርፋሳ እርሻ መድረሱን ያመለክታል፡፡








ስእል 25: ኡርጂ ለሚ ከNASA Observatory ሲታይ

### 5.2.2 ኡርጂ ቡሳን (Pleiades)


ኡርጂ ቡሳን ሠባት እህትማማቾች ኡረጂ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ለመሬት በጣም ቅርብ የሆኑና በጫምሣ ወር የሚታዩ ናቸው፡፡




ስዕል 26: ኡርጂ ቡሳን ከNASA Observatory ሲታይ

### 5.2.3 ኡርጂ ባካልቻ (Aldebaran)

ኡርጂ ባካለቻ በቡፋ ወር ላይ ይታያል፡፡





ስዕል 27: ኡርጂ ባካልቻ

### 5.2.4 ኡርጂ  አልጋጂማ (Bellatrix)

ኡጂ አልጋጂማ በጣም ከባድ ስትሆን የትልቅ ጠንካራ ሴት ምልክት ናት፡፡ ይህ ኮከብ በስተደቡብ ሰማይ በኩል ፀሀይ

ከጠለቀች በኃላ የሚታይ ናት፡፡ ኡርጂ አልጋጂማ በሰኔ ላይ የሚታይ ሲሆን ይህም ቀን እንዲራዘም የሚያደርግ ነው፡፡





ስዕል 28: ኡርጂ አላጋጂማ እና ፀሀይ ከቀኝ ወደግራ ከNASA Observatory ሲታይ

### 5.2.6 ኡርጂ ቡሳ (Sirius)

ኡርጂ ባሳ በመጀመሪያ ክረምት ላይ የሚታይ ይህም ምድር ተክል ለማብቀል ስትዘጋጅ ያሳያል፡፡ ይህም የክረምት ውሃ ሙላትን ለማባሰር በክረምት ጎርፍ ጊዜ የሚታይ ነው፡፡ ወደ ንጋት አካባቢ ሰማይ ላይ ስትታይ የክረምት ጊዜ መድረሱን የሚያመለክትና የውሃ መሙላት የምታሳውቅ ናት፡፡

ኡርጂ ባሳ የውሻ ኡርጂም ስትባል የውሾች መራቢያ ጊዜንም ታሳያለች፡፡ እንዲሁም ሴት ልጅ አግብታ ልጅ የምትወልድበትን

ጊዜ ያመለክታል፡፡ ስትታይም ንፁህ ከሆነ ጥሩ እድልን ያሳያል፡፡







ስዕል 29፡ ኡርጂ ባሳ ከNASA Observatory ሲታይ

### 5.2.7 ኡርጂ ዋላ (Saiph)

ኡርጂ ዋላ የእረሻ ጊዜ መቃረብን የሚያሳይና የእርሻ መሣሪያዎች የሚያዘጋጁበት ጊዜ ነው፡፡ በቀኝ እግር ጉልበት የሚመሰል ኡርጂ ኮሲሆን ጉልበት ለእርሻ ጠንክሮ የሚዘጋጁበት ጊዜ ነው፡፡



ስዕል 30: ኡርጂ ዋላ ከNASA Observatory ሲታይ

## 5.3 ወቅቲና ወራት

Dha-ሀ 12 ወራት ሲኖረው ይህም በአራት ወቅቲ ይከፈላል፡፡

**ሰንጠረዥ 1፡ አራቱ ወቅቲ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቢራ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር |
| በጋ | ታህሳስ | ጥር | የካቲት |
| በልግ | መጋቢት | ሚያዚያ | ግንቦት |
| ክረምት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሀሴ |

የእያንዳንዱ ወር ከጨረቃና ከኮከብ ጋር በአንድ ላይ ይታያል፡፡

ሰንጠረዥ 2፡ 12ቱ የDha-ሀ ወራት

| የወር ስም | የDha-ሀ ኮከብ | የእንግሊዝኝ ስም |
|---|---|---|
| 1. መጋቢት | ለሚ | Triangulum |
| 2. ሚያዚያ | ቡሳን | Pleiades |
| 3. ግምቦት | ባካልቻ | Aldebaran |
| 4. ሰኔ | አልጋጂማ | Belletrix |
| 5. ሐምሌ | አርባ ጋዱ | Central Orion |
| 6. ነሐሴ | ባሳ | Sirius |
| 7. መስከረም | ኀበን ጨረቃ | |
| 8. ጥቅምት | ግማሽ ጨረቃ | |
| 9. ህዳር | ኑሳ ጨረቃ | |
| 10. ታህሳስ | ትልቅ ጨረቃ | |
| 11. ጥር | መካከለኛ ጨረቃ | |

| | | |
|---|---|---|
| 12. የካቲት | ትንሽ ጨረቃ | |

እንደዚ Dha-ሀ የአመት አዲስ ወር በቢቶቴሳ ሲጀመር ቀኑ ደግሞ "ቢታ ቃራ" ይባላል፡፡ ይህም ጨረቃ ከኡርጂ ለሚ ጋር የሚታይ ይሆናል፡፡ ከዚህ በኃላ እያንዳንዱን ቀን እስከ 27 ወደ ታች መከተል ሲሆን በስተመጨረሻም ሦስት ቀናት ይደገማሉ፡፡ ከዛ የሚቀጥለው ወር የሚጀመረው ጨረቃ ከኡርጂ ቡሳን ጋር ሲትወጣ ይሆናል፡፡

ይህም ቢቶትሳ ወር ከጀመረ 29.5 ቀን በኃላ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ የ27 ቀናት ስም ብቻ ስላለሆነ የቀሩት ከመጀመሪያው ወስደው ሲጠሩ ይህም ከሁለት ሦስት ወራት ይፈጃል፡፡ ሶስተኛው ወር ጨረቃ ከኡርጂ ባካልቻ ጋር ሲትወጣ ነው፡፡ ይሁንና ጋን ቀሪ ስድስቱ የdha-ሀ ኡርጂዎች አሁን ባለችው ኢትዮጵያ ውስጥ አይጡም፡፡ ስለዚህም በወራት መጀመሪያ የdha-ሀ ኡርጂ ሳይታዩ በጨረቃ ብቻ በመጠቀም ይቆጥራሉ፡፡

***********

ማራባ የረቢ ነው !

***********

ገዳ ለመሆን ..... ሰፉን ጠብቁ !

ጋታማ እንዳትሆኑ ከሀራሙ እና ከጫጳና እራሳቹን ጠብቁ !

# ዋቢ መጻህፍት

[1] Megerssa, Gemetchu. 1993. Knowledge, Identity, and the Colonizing Structure: The Case of the Oromo in East and Northeast Africa, (Ph.D. diss.: University of London, School of Oriental and African Studies.)

[2] Buatovich, Alexander. 2000. Ethiopia through Russian Eyes: Country in Transition, translated by Richard Seltzer, (Lawrenceville, NJ: The Red Sea Press).

[3] Bulcha, Mekuria. 1996. "The Survival and Reconstruction of Oromo National Identity," Being and Becoming Oromo. Historical and Anthropological Enquiries, Eds. P. T. W. Baxter,

[4] de Loo, Joseph Van. 1991. Guji Oromo Culture in Southern Ethiopia: Religious Capabilities in Rituals and Songs, (Berlin: Berietrich Reimer Verlag).

[5] de Salviac, Martial. 2005 [1901]. An Ancient People, Great African Nation, translated by Ayalew Kano, (East Lansing, Michigan).

[6] Hinnant, John. 1978. "The Guji: Gada as a Ritual System," in Age, Generation and Time: Some Features of East African Age Organisations, edited by P.T.W. Baxter and Uri Almagor, (London: c. Hurst & Company).

[7] Kassam, Aneesa. 2007. "The Oromo Theory of Social Development," Between the State and Civil Society in Africa: Perspective on Development, T. Mkandawire and E.E. Osagahae, (eds.), (Dakar: CODESRIA).

[8] Jalata, Asafa. 2007. Oromummaa: Oromo Culture, Identity and Nationalism, (Atlanta: Oromia Publishing Company).

[9] Jalata, Asafa. 2012. Fighting against the Injustice of the State and Globalization: The African American and Oromo Movement, second edition, (New York: Palgrave Macmillan).

[10] Jan Hultin, Alessandro Triulzi (Uppsala: Nordiska Afrikainstitutet). de Salviac, Martial. 2005 [1901]. An Ancient People, Great African Nation, translated by Ayalew Kano, (East Lansing, Michigan).

[11] Kelly, Hilarie Ann. 1992. From Gada to Islam: The Moral Authority of Gender Relations among the Pastoral Orma of Kenya, Ph.D. dissertation, University of California, Los Angeles, 1992).

[12] Baxter, P. T. W. 1990. "Oromo Blessings and Greetings," in A. Jacobson-Widding and W. Van Beek, (eds.), the Creative Communion: African Folk Models of Fertility and the Regeneration of Life, (Uppsala: Acta Universitatis Upsalienis).

[13] Knutsson, K. E. 1967. Authority and Change: A Study of the Kallu Institution among the Macha of Galla of Ethiopia, (Gotenborg: Ethnografiska Museet), pp. 37-42.

[14] Kumsa, Kuwee. 1997. "The Siiqqee Institution of Oromo Women," The Journal of Oromo Studies 4 (1 & 2).

[15] Bartels, Lambert. 1990. Oromo Religion, Berlin: Dietrich Reimer Verlag).

[16] Blackhurst, Hector. 1996. "Adopting an Ambiguous position: Oromo Relationships with Strangers," Being and Becoming Oromo: Historical and Anthropological Enquiries, (Uppsala: Nordiska Afrikainstitutet).

[17] Waqayyo, Qabbanee. 1991. "Women's Influence in Oromo society During the Period of Gada Rule," Waldhaansso: Journal of the Union Oromo in North America, August, vol. Xvi, no.

[18] Blackhurst, Hector. 1978. "Continuity and Change in the Shoa Gada System," Age, Generation and Time, ibid, pp. 245-267.

[19] Baxter, P. T. W. 1978. "Boran Age-Sets and Generation-Sets: Gadaa, a Puzzle or a Maze?" Age, Generation and Time, edited by P. T.

W. Baxter and Uri Almagor, (London: C. Husrst & Company), pp. 151-182.

[20] Baissa, Lemmu. 1993. "The Political Culture of Gada: Building Blocks of Oromo Power," paper Presented at the Oromo Studies Association Conference, University of Toronto, Canada, 31 July-1, August.

[21] Baissa, Lemmu. 2004. "The Oromo Gadaa System of Government: An Indigenous African Democracy," edited by Asafa Jalata, State Crises, Globalisation and National Movements in Northeast Africa, (New York: Routledge, 2004), 101-121.

[22] Asante, M. K. 1988. Afrocentricity, (New Jersey: Africa World Press, Inc.).

[23] Asante, M. K. 1990. Kemet, Afrocentricity and Knowledge, (Trenton, NJ: The African World Press).

[24] Baxter, P. T. W. 1979. "Boran Age-Sets and Warfare, in Senri Ethnological Studies 3, 19, pp. 69 95.

[25] Lepisa, Dinsa. 1975. "The Gada System of Government and Sera Cafee Oromo," (LLB. Thesis, Addis Ababa University).

[26] Lewis, Herbert S. 1966. "The Origins of the Galla and Somali," Journal of African History, vol. 7, no. 1).

[27] Luling, Virginia. 1965. "Government and Social Control among Some Peoples of the Horn of Africa," (M.A. Thesis: The University of London).

[28] Braukamper, Ulrich. 1980. "Oromo Country of Origin: A consideration of Hypothesis," Proceedings of the Second International Conference, April, p. 25.Ibid, pp. 243-44. Bulhan, Hussein Abdilahi. 1985.

[29] Ehrest, Christopher. 1976. "Cushitic Prehistory," M. L. Bender, (ed.), the Non-Semitic Languages of Ethiopia, (East Lansing: Michigan State University).

[30] Etefa, Tsega. 2008. "Pan-Oromo Confederations in the Sixteenth and Seventeenth Centuries," The Journal of Oromo Studies 15 (1): 19-40.

[31] Frantz Fanon and the Psychology of Oppression, (New York: Plenum Press).

[32] Gololcha, Tedecha. 1998. The Politico-Legal System of the Guji Oromo, (LLB. Thesis: Addis Ababa University).

[33] Greenfield, Richard Greenfield and Mohammed Hassen. 1980. "Interpretation of Oromo Nationality," Horn of Africa, vol. 3, 3.

[34] Haberland, Von Eike. 1963. Galla Sud-Athiopiens, (Stuttgart: Verlag W. Kohlhammer), Hambly, Wilfrid D. 1930. Ethnology of Africa, (Westport: Negro University Press).

[35] Hassen, Mohammed. 1990. The Oromo of Ethiopia: A History 1570-1860, (Cambridge: Cambridge University Press).

[36] Holcomb, B. 1999. "Oromo in the World Community," The Journal of Oromo Studies 6 (1 & 2): 1-48.

[37] Holcomb, B. and S. Ibssa. 1990. The Invention of Ethiopia: The Making of Dependent Colonial State in Northeast Africa, (Trenton, NJ: The Red Sea Press).

[38] Holcomb, Bonnie K. 1991. "Akka Gadaatti: The Unfolding of Oromo Nationalism-Keynote Remarks," Proceedings of the 1991 Conference on Oromia, University of Toronto, Canada, 3-4 August, 1-10.

[39] Holcomb, Bonnie K. 1991. "Akka Gadaatti: The Unfolding of Oromo Nationalism-Keynote Remarks," Proceedings of the 1991 Conference on Oromia, University of Toronto, Canada, 3-4 August, 1-10.

[40] Holcomb, Bonnie K. 1993. "Ideological Bases for Oromo Empowerment," Paper Presented at the Oromo Studies Association Annual Conference, University of Toronto, Canada, 31 July -1 August 1993.

[41] Huntingford, G.W. B. 1955. The Galla of Ethiopia, the Kingdom of Kafa and Janjero, London.

[42] Huqqa, Gollo. 1998. The 37th Gumii Gaayo Assembly, (Addis Ababa: The Norwegian Church Aid).

[43] Ibssa, Sisai. 1992. "Implications of Party and Set for Oromo Political Survival," Paper Presented at the 35th Annual Meeting of African Studies Association, Seattle, Washington, Nov. 20-23.

[44] Jalata, Asafa. 1998. Oromo Nationalism and the Ethiopian Discourse: The Search for Freedom and Democracy, edited, (Lawrenceville: The Red Sea Press).

[45] Legesse, Asmarom. 1987. "Oromo Democracy," Paper Presented to the Conference on the Oromo Revolution, Washington, D. C., August 16.

[46] Zelalem Tesfaye Sirna. Ethiopia: When the Gadaa Democracy Rules In A Federal State: Bridging Indigenous Institutions of Governance to Modern Democracy. Masters of Philosophy, University of Tromsø, 2012.

[47] Ta'a, Tesema. 1986. "The Political Economy of Western Central Ethiopia: From the Mid-16th to the Early-20th Centuries," (Ph. D. Dissertation, Michigan State University, 1986). The Journal of Pan African Studies, vol.5, no.1, March 2012

[48] Melba, Gada. 1980. Oromia: A Brief Introduction, (Fifinnee: Oromia). P. T. W. Baxter, Jan Hultin, and Alessandro Triulzi (Uppsala: Nordiska Afrikainstitutet).

[49] Legessee, Asmarom. 2006 [2000]. Oromo Democracy: An Indigenous African Political System, (Lawrenceville, NJ: The Red Sea Press).

[50] Legesse, Asamrom. 1973. Gadaa: Three Approaches to the Study of African Society, (NewYork: Free Press).

[51] Doyle, Laurance R. The Borana Calendar REINTERPRETED. Current Anthropology. Physics and Astronomy Department, University of

California, Santa Cruz, at NASA Ames Research Center, Space Sciences Division, M.S., retrieved: 7 April 2010.

[52] Asmarom Legesse. Gada Three Approaches to the Study of African Society. The Free Press A Division of Mc Millan Co. Inc, 1973



View publication stats